ትግላችን [illegible]
ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መጽሔት
በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ
Prepared by the Ethiopian Students Union
in Europe

Vol.9 No. 1 P.O. Box 3193 Stockholm, Sweden ቅጽ ፱

# በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ፳፩ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርትና የፖለቲካ ውሳኔ

ቁጥር ፩

September 1981 መስከረም ፲፱፻፸፬

## በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 21ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 21ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ በቤልጂየም ሀገር በሉቨን ከተማ ከኦገስት 3-8—10-8-81 እ.ጎ.አ ከፍተኛና የሞቀ የትግል መንፈስ በተሞላበት ሁኔታ ተካሂዷል።

ይህ 21ኛ ጉባኤ የተከናወነው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች/በልዩ ልዩ አውሮፓ ሀገሮች ያሉ ቅርንጫፍ ማህበራት/እንደሆነ ቢታወቅም በዚህ ጉባኤ ላይ የነበሩ ቅርንጫፍ ማህበራትና የጥናት ክበባት የሚከተሉት ነበሩ፡—

1 .የስዊድን ቅርንጫፍ ማህበር
2 ሆላንድ
3 ምዕራብ ጀርመን
4 እንግሊዝ
5 ዩጎዝላቪያ
6 ቤልጂየም
7 ፈረንሳይ
8 የሶቭየት ሕብረት ነበሩ።

3-8 የእኪተማ 21ኛ ጉባኤ ተከፈተ።በዚህ ዕለት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የመክፈቻ ንግግር ከማድረጉም በላይ ይህ 21ኛ ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት እሲተማን እዚህ ከፍ ያለ የትግል አቋም ደረጃ ላይ ያደረሱትን፣በትግል ሜዳ የተሰውትን፣በእሥር ቤት ተወርውረው ኢሰብዓዊ ድርጊት የሚፈፀምባቸውንና ለብሔራዊ ነፃነትና ክብር፣ለዲሞክራሲና ለብሔረሰቦች እኩልነት ሲሉ ከሰፊው ሕዝብ ጎን ያለማወላወል ለዘላቂውና ለመራራው ትግል የሚታገሉትን በሙሉ በታላቅ ስሜት አስታውሶቸዋል።

ከዚህ በመቀጠል የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ስለ አገር ቤት ሁኔታና ስለ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ልዩ ሪፖርት በማቅረብ ሰፋ ያለና ጠቃሚ ትንተና አቅርቧል።በዚሁ በሥራ አስኪያጅ ሪፖርት ላይ ቤቱ ሰፋ ያለ ውይይት በማድረግ የቀረበውን ትንተና ከተጨባጭ የአገር ቤትና የአለም አቀፍ ሁኔታ ጋር አገናዝቧል።በጉባኤው መክፈቻ ዕለትና በቀጠሉት ቀናት ከልዩ ልዩ ድርጅቶችና ሀገሮች ለጉባኤው የተላኩ የአንድነት መግለጫዎች ተሰምተዋል።

ለጉባኤው የደረሱት የአንድነት መግለጫዎች የሚከተሉት ነበሩ፡—

1 ከመላ ኢትዮጵያ ሶሺሊስት ንቅናቄ (መ.ኢ.ሶ.ን)
2 ከኢትዮጵያ አብዮታዊ ወጣቶች ንቅናቄ (ኢ.አ.ወ.ን)
3 ከኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢ.ሴ.አ.ን)
4 ከኩርድ ተማሪዎች ማህበር በአውሮፓ (ኩ.ተ.ማ)
5 ከአውሮፓ የኢትዮጵያ ሴቶች ዲሞክራቲክ ማህበር (አ.ኢ.ሴ.ዲ.ማ)
6 ከዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ሕብረት (ዓ.አ.ኢ.ተ.ማ.ሕ)
7 የተባበሩት ተራማጅ አንድነት ማህበር በሰሜን አሜሪካ
8 በሃይደል በርግ ዩኒቨርሲቲ የፋካልቲ ተወካዮች ጠቅላላ ጉባኤ ም.ጀር መን
9 Membre du Parlement Europeé/Belgium
10 Parti du travall de Beliqique /bruxelles
11 Latinamerika komitee München (LAK-) W. Germany
12 Amnesty International Vlaandeven/Belgium
13 Komaunisttische studengruppen/Stuttgart
14 Kommunistische studentgruppen-Deutschland
15 International Youth and student movement for the United Nations.

16 Oxfan - Belgique
17 Studie-en documentatie centrum (S.E.V.I) /Bruxelles
18 Federation of Iranien student in Sweden member of CIS Stockholm
19 The Flemisch Lenten campaigh in Belgium (African desk)

ልዩ ልዩ የትግል አንድነት መግለጫዎች ከተነበቡ በኋላ ጉባኤውን የሚመሩ ሊቀመንበርና ፀሐፊዎች፣የዓመቱን ወጪና ገቢ እንዲሁም ጠቅላላ የማህበሩን ንብረት የሚመረምሩ ኦዲተሮችና የውሳኔ አርቃቂዎች ምርጫ ተከናውኗል::

የመጽሔት ቦርድ ሪፖርት ተሰምቶ በዚህም ላይ ጠቃሚ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ጠቅላላ ጉባኤው ወደ ዋናው አበይታዊ ሥራው ማለትም በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ ወደሚወያይበት አጀንዳ ተሸጋገረ::

በዚህ ዕለት በጠቅላላ ጉባኤው ፀድቆ ለውይይት የቀረበው የጥናት አጀንዳ ከዚህ የሚከተለው ነበር:—

<u>በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር</u>

<u>ለ21ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበ የጥናት ረቂቅ</u>

<u>ክፍል አንድ</u> :— <u>የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ</u>
ሀ— ዛሬ ኢትዮጵያ በምትገኝበት ክልል ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች አመጣጥ
ለ— የኑሮ የአስተዳደርና የኢኮኖሚ ቅርፃቸው
ሐ— ያደረጉት እንቅስቃሴና ያቋቋሟቸው ከተሞች
መ— የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አፈጣጠርና ስለሚኖሩበት ሕዝቦች :

<u>ክፍል ሁለት</u>:— <u>የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ</u>
ሀ— ፖለቲካዊ
ለ— ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ባህላዊ ኑሮ
ሐ— ሚሊተሪያዊ

<u>ክፍል ሦስት</u>:— <u>የግንባር ጥያቄ</u>
ሀ— የግንባር አስፈላጊነት ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር
ለ— በግንባር ውስጥ የሚሰለፉ ኃይሎች
ሐ— ለሚመሠረተው ግንባር መሟላት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች

<u>ክፍል አራት</u>:— <u>ስለ ብሔር</u>
ሀ— የብሔር ምንነት
ለ— በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች የደረሱበት የእድገት ደረጃ

<u>ክፍል አምስት</u>:— <u>የኢትዮጵያ አብዮት ድክመት</u>
ሀ— የሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ጥንካሬና ድክመት
ለ— የድክመት ምንጮች
ሐ— የአብዮቱ መጠቃት በወጣቱ እንቅስቃሴ ላይ ያስከተለው ድክመት
መ— ከዚህ ድክመት ለመወጣት ተግባራችን ምን መሆን አለበት

በዚህ አጀንዳ ላይ ከ3-8 እስከ 10-8-81 ውይይት ከተደረገ በኋላ የውሳኔ አርቃቂ ኮሚቴው ጠቅላላ ጉባኤው በአካሄደው ውይይት ላይ በመመርኮዝ ረቂቅ ውሳኔ አቅርቦ በዚህ ረቂቅ ውሳኔ ላይ ልዩ ልዩ ማሻሻያዎች ተረቡና በቂ ውይይት ከተደረገበት በኋላ አባላት በሙሉ ተሰበሰቡበት በጠቅላላ ቢቶ በምንት ፀድቆ (በአንድ ሰው ተቃዋሚ) ጉባኤው የተጠበሰውን ውሳኔ በጋለ ጭብጨባና በከፍተኛ የትግል መንፈስ ተቀብሎታል::



ከዚህ በኋላ በ10-8-81 የቅርንጫፍ ማህበራት ሪፖርት በተራ ቀርቦ ውይይት ከተካሄደባቸው በኋላ ለሚመጣው ዓመት የሥራ አስኪያጅ፣የመጽሔት ቦርድ በመምረጥ ጉባኤው ዓመታዊ ሥራውን አከናውኗል::

—————— // ——————

## <u>የአኢተማ 21ኛው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔ</u>

<u>መግቢያ</u>

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሰፊው ሕዝብ ለእኩልነት፣ለብሔራዊ ነፃነትና ለሰብአዊ መብቱ ከፍ ያለ ትግል ያካሂዳል::ሆኖም በኢትዮጵያ ምድር ላይ ያንሰራራው ወታደራዊ መንግሥት ይህንን ትክክለኛ ማንም ኃይል ሊገታው የማይችለውን ሀቅ ለመጣል በበኩሉ ከፍ ያለ ጥረት በማድረግ በቀን ተራማጆች፣በአገር ወዳዶችና በብሔረሰብ እኩልነት መብት ታጋዮች ላይ ይህ ነው የማይባል የሞት፣የእሥራትና የስደት ዘመቻውን አስፋፍቷል::

ወታደሩና አጋሮቹ የውጭ መንግሥታት ያለ የሌላቸውን ኃይልና ሀብት በማፍሰስ ይህንን ትክክለኛ ትግል ለመግታት ቢፍጨረጨሩ አገሪቱን በከፍተኛ የፖለቲካ፣የኢኮኖሚ፣የማህበራዊ ኑሮ ችግር ውስጥ ከተዋታል::ግድያ ረሀብና እሥራትን የሕዝቡ ዕጣ አድርገውታል::

የኢትዮጵያ ሕዝቦች —ሀ— ብለው ትግል የጀመሩበት የዲሞክራሲ ጥያቄ እንኳን በሽታው ጠፍቷል::ዲሞክራሲ በሌለበት፣ፀረ—ዲሞክራሲ በሚል እንቆቅልሽ ሕዝቡ ይሸነገላል::ሰፊው ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር የታገለለት የመሬት ጥያቄ ምንም እንኳ በአዋጅ ደረጃና ከዚያም ለተከታተሉት 3 ዓመታት በሥራ ለመተርጎም ትግል ቢደረግም ዛሬ የወታደሩ መንግሥት መሬቱን በመንግሥት እርሻ፣ገበሬውን በሕብረት ሥራ ስም እንደገና እየነጠቀው ይገኛል::

የወታደሩ መንግሥት ሕዝቡ ለሚያነሳው የረሀብ ጥያቄ፣ሕዝቡ ለሚያነሳው የእኩልነት ጥያቄ መልስ ከማጣቱ የተነሳ ረሀብ ያመጣው እንደ ነጋዴ ነው፣ሌላ ግዜ ደግሞ ምሑሩ ነው፣እንዴ ገበሬ ነው፣እያለ እንደ አበደ ውሻ ሁሉን ይነክሳል::ለሚቀርብለት የእኩልነት ጥያቄ፣ዲሞክራሲያዊ ይዘት ያለው ውይይት ከመፈለግ ይልቅ፣ከደሃው ሕዝብ ጉሮሮ እየነጠቀ በሚገዛው የሶቭየት መሣሪያ የብሔረሰቦችን ትግል አጠፋለሁ ብሎ ከአዋቂ እስከ ሕፃናት ከአውራጃ እስከ ቀበሌ በሕዝቡ ላይ ጦርነት በማወጅ በሀገሪቱ አራት ማዕዘን የሕዝብ እልቂት ይዟል::ከዚህ ጠቅላላ የመንፈስ ጭንቀት የተነሳ ገበሬው የማምረት፣ነጋዴው ልዩ ልዩ ንግድ ማስፋፋት፣ምሁሩ የመፍጠር ችሎታው፣ሠራተኛው የመሥራት ፍላጎቱ ተገቷል::

ከዚህ በተረፈ ሀገሪቱ በሶቭየት ሕብረት ቀጥተኛ ሥር ወድቃለች::የወታደሩ መንግሥት ቀፍው እንደሚ የመንግሥት ሕልውናው አልቆለታል::የጦር፣የፀጥታና የአስተዳደር ክፍሎች የሚመሩት በሶቭየትና በጭፍሮቻቸው አማካኝነት ነው::ሀገሪቱ የምታደርገው ማንኛውም ዓይነት የዓለም አቀፍም ሆነ አገር አቀፍ እንቅስቃሴ በሶቭየት ሕብረት መሪነት ነው ብንል ስህተት አይሆንም::

እንግዲህ አገራችን በዚህ ሁኔታ ውስጥ በምትገኝበት ወቅት ይህ 21ኛ ጉባኤ የሀገሪቱን ሁኔታ አጥብቆ ከመረመረ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን ተጨባጭ ውሳኔ አስተላልፏል::

### <u>•የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መሠረታዊና ዋና ዋና ቅራኔዎች</u>

በአንድ አገር ውስጥ የሚካሄደውን የሕዝቦች ትግል በትክክል ለመረዳት፣ትግሉን ለማቀነባበርም ሆነ በትግሉ ውስጥ ለመሰለፍ በግድ በአገር ውስጥ ያሉትን የመደቦች አሰላለፍ፣በመካከላቸው ያለውን ቅራኔ ለይቶ ማወቅና ጠላትና ወዳጅን መለየት የአንድ ታጋይ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ተቀዳሚ ግዴታው ነው::ይህን ዘዴ አኢተማ ለብዙ ጊዜ በትክክል ተጠቅሞበታል፣አሁንም ይጠቀምበታል::

መቼም የቅራኔ አደራደር ካለው ትግል ጋር የሚዛመድና ለትግሉ አቅጣጫ ሰጪ እንደ መሆኑ መጠን በየጊዜው እንደ ትግሉ ዓይነት ይለዋወጣል::ልዩ ልዩ መደቦች የሕብረተሰብ

ከፍሎች በአንዱ በተወሰነ ወቅት ከሕዝብ ጐን ቆመው ወይም ተሰልፈው ቢታገሉ፣የሕዝብ ወገን ቢባሉ፣በሌላ ወቅት ለጥቅማቸው ሕዝብን ቢፃረሩ የሕዝብ ጠላት ይሆናሉ::በአገራችን ከፊል ከበርቴ ከፊል ፊዩዳል የነበረውን መንግሥት ለመጣል(ሥርዓቱን ለመጣል)ተባብረው ከሕዝብ ጐን ከቆሙ ኃይሎች መካከል በዚህ ሥርዓት መቃብር ላይ ነፃና ዲሞክራቲክ አስተዳደር ለመፍጠር በተደረገውና በሚደረገው ትግል ደግሞ ከነዚህ ድርጅቶች ወይንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ተገምቦ የሕዝብ ጠላት ሆኖ ቀርቷል::

ቅራኔ፣በተለይም አብዮታዊ ሁኔታን ለመገምገም የሚረዳ ቅራኔ፣በመደቦች መካከል የሚከሄድ ቅራኔ እንጂ በግለሰቦች መካከል የሚደረግ ሽኩቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ በመደብ ከፍለን በንመለከትና የእያንዳንዱን መደብ ወዳጅና ጠላት፣የእያንዳንዱን መደብ የእርስ በርስ መበሻብ አጠቃላይ ወስደን መሠረታዊና ዋና ዋና ቅራኔ ለማውጣት ይቻላል::

<u>የከበርቴው መደብ</u> :— የኢትዮጵያ ከበርቴ እንደ ሌሎች ሀገሮች ከበርቴ የከበርቴ ዓይነትጠሙሉ አድጎና ተስፋፍቶ አይገኝም::ሆኖም ተስፋፍቶ የነበረው የመሬት ከበርቴ ቢሆን በ74 አብዮት ስለተመታ በሱ በኩል ስለ አስተያየት በዚህው ብዙ ልናተኩር አሁን አናልፈዋለን። በአሁኑ ወቅት በአገራችን ተስፋፍቶና ደርጅቶ ልዩ ልዩ በማለት በበዝበዛ ላይ የተሰማራው የቢሮ ከበርቴው ሆኖ እናገኘዋለን::ምንም እንኳ ከኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ ይህ መደብ ከመሬት ከበርቴው ጐን እያደገ የመጣ ቢሆንም እንደአሁኑ "ቁንጮ ተሰትኖ"ለይቶለት በገዢ መደብነት ታውቆ አያውቅም::አሁን ባለንበት ወቅት ግን ይህ መደብ ከሌሎች አንዳንዱ የሕብረተሰብ ክፍሎችና ከውጭ ኃይሎች ጋር በማበር ሥልጣን ጨብጦ፣ተደራጅቶ ሕዝቡን የሚበዘብዝ የሕዝብ ጠላት የሆነ መደብ ነው::

<u>ብሔራዊ ከበርቴው</u> ግን አሁንም (ምንም እንኳ ከፋኛ በመታም) ከዚህ ነፃ በሆነ መንገድ ለመኖር ትግል ያደርጋል::ወትሮም በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በዝበዛ ማደግ ባለመቻሉ ኃይሉና ብዛቱ የተወሰነ ነበር::በአሁኑ ጊዜም ብዛውንበሆነው ባልሆነው በየአሥር ቤቱ በጫ ገር ንብረታቸውንና ቤታቸውን ቢሮ ከበርቴው ቀርጣ አድርጉታል::በብሔራዊ ከበርቴውና በቢሮ ከበርቴው መካከል የጥቅም ግጭት አለ::ብሔራዊ ከበርቴው ነፃ የኢኮኖሚ እድገት ቢፈልግ፣የአቀባባይ ከበርቴው፣የከፍተኛ መኮንኖችና የሲቪል ቢሮክራቶች ከበሽየት ሕብረትና ተቀጢሳዎች ጋር የጥቅም ሸርካ በመሆን ይተባበራሉ::

<u>ንዑስ ከበርቴው</u>:— በአገራችን ንዑስ ከበርቴ ብለው ከሚመደቡ የሕብረተሰብ ክፍሎች አብዛኛው ዝቅተኛው ነጋዴ፣መምህር፣ዝቅተኛ ቢሮ ሠራተኛው፣ወታደሩ፣ተማሪው ወዘተ ይገኙበታል::ይህ መደብ እንዲላ በቢሮ ከበርቴውና በከፍተኛ መኮንኖች ወይም በጊዜው ገዢ መደቦች ይጠቃናል::የዛሬው የገዢ መደብ የዚህን መደብ ስፋትና ጥሳች ስለሚያውቅ በደገብ ይጠቀነዋል::በሁለቱ መካከል በዛሬው ወቅት ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ ደረጃ ደርሷል::

<u>አርሶ አደሩ</u>:— ከፍተኛ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያጠቃልል (ወይም 90 በመቶ) ይህ መደብ ነው::ይህ መደብ ምንም እንኳን ከመሬት አዋጁ ወዲህ በትግሉ ባገኘው መብት በመጠቀም አርሶ ሆኑን ለመሙላት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ከመሬት አዋጁ ጋር መምጣት የነበረበት የዲሞክራቲክ መብት ወያኔ፣የማኅበራዊና የሕብረት ሥራ፣የሠርቶ ማሳያ ጣቢያ ወዘተ አብረው በለመገኘታቸው ትናንት ያገኘውን መሬት ዛሬ በጠሊ መሪዎች "ለመንግሥት እርሻ" "ለሕብረት እርሻ" በማለት ልዩ ልዩ ምክንያት በመሰጠት አከፊተው ኋርር ውስጥ ዱንጋይ ለመቆር ቆር ተዘጋጅተዋል::አንዳንዱ ሰው በታዎች ለመንግሥት ብለው መነጠቃቸውን ማንም የሚያውቅ ነው::ይህም መደብ የአሁኑን የገዢ መደብ አጥብቆ ይቃወማል:: ይጠላዋል:: ይታገለዋልም::

<u>ወዝአደር</u>:— የኢትዮጵያ ወዝአደር በኢንዱስትሪ አንደገፉ አገሮች ብዛቱ ከፍተኛ ባይሆንም በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ በቂ ሚና የተጫወተና ወደፊትም ሊጫወት የሚችል ኃይል ነው::ወዝአደሩ ከዚህ በፊት 74—75—76 ቀምበት ከነበረው የዲሞክራሲ ጥሳንቄል ብዙ ተምሯል::ጠላትና ወዳጅን ሊለይ የሚችል ኃይል ብቻ ባይሆን የነፃ ድርጅትን ጥቅም ስለሚያውቅ ለአሁኑ ነፃነት ገፈፊ ለሆነው መንግሥት ተንበርክኮ መገዛትን አጥብቆ ይቃወማል::በልዩ ልዩ በነኩል ምክንያት ሥራ በማጣታቸው ብዙ ወዝአደሮች ያለ ዕለት ጉርስ ይገ



ከፈተታሉ፣ብዙ ቤተሰብ ተበትኗል። በሥራ ላይ ሰሰሙ እንኳ ያለው፡የሚያገኘው ደመወዝ ከኑሮ ውድነት ጋር ስለማይጣጣም <u>ከእጅ ወደ አፍ</u> ኑሮው አቀተታል::በወዝአደሩና በዛሬው ገዢዎች መካከል ከበዱና የማይታረቅ ቅራኔ አለ::

ከዚህ በመነሳት <u>21ኛው የአኪተማ ጠቅላላ ጉባኤ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መሠረታዊ ቅራኔ በከፍተኛ መኮንኖች፣በወታደራዊ የቢሮ ከበርቴው መንግሥት፣በጣልቃ ገቡ የውጭ ኃይል (የበሽየት ኃይል) በአንዱ በኩልና በሌላ በኩል በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ነው ብሎ ያምናል::</u>

የውጭ ኃይሎች <u>በአገራችን ውስጥ ጣልቃ ገብተው የራሳችንን ዕድልና ፍላጎት ፈጣሪና በለመበት እንዳገሆን ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶች ጋር ስለቆሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ናቸውና በአንደኛ ደረጃ ያሉ የሰፊው ሕዝብ ጠላቶች ናቸው ብሎ ጉባኤው ተቀብሏል:: የ2ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ በመመሥረት እነዚህን የሕዝብ ጠላቶች ከሕዝብ ጐን በመሰለፍ ይታገላቸዋል::</u>

## 2.<u>ስለ አምባገነኑ የወታደር መንግሥት</u>:—

የዛሬ ዓመት በ20ኛው ጉባኤችን እንደአስቀመጥነው ሁሉ አሁንም የወታደሩ መንግሥት <u>የቢሮክራቲክ መንግሥት</u> ነው::<u>ኢሱም በመሠረቱ የሚመራው በከፍተኛው የወታደርና የሲቪል ቢሮክራቶች ክሊክ</u> ነው::ከሁለቱ መካከል የመንግሥቱን መኪና የጨበጠው የከፍተኛው መኮንኖች ቡድን ነው::ከዚህ ውስጥ ደባል ሆኖ የሚገኘው የሲቪል ቢሮክራሲው ክፍል, ተሳላኪና ትዕዛዝ አስፈጻሚ እንጂ የወሳኝነት ሥራና ሚና የለውም::ሆኖም የሲቪል ቢሮክራሲው ክፍል በአንዱ በኩል ዛሬ ጠንክሮ የሚገኘውን የከፍተኛ መኮንኖች ክሊክ ሊቋቋም ስለማይችል፣በሌላ በኩል ደግሞ የወታደሩ አገዛዝ ፀረ—አብዮተኛነትና ትምክህተኛነት፣ፀረ—ሕዝብነት ለእርሱም ስለአመቸው ከአለው አገዛዝ ጋር ተቻችሎ ብቻ ሳይሆን አገዛዙን አጅቦ ለማገልገል ዝግጁ ነው::

ይህን የገዢ መደብ ዓይነተኛ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ባህሪዎች ጥቂቶቹ ፀረ—ዲሞክራቲክነቱ፣ትምክህተኛነቱ፣ብሔራዊ ከህደቱ ናቸው::የራሱን ጥቅም ለመሰብሰብ ሲል በከተማና በገጠር በመንግሥት እርሻ ስም፣በህብረት ንግድና በመንግሥት ንግድ ስም የሚያደርገው የኢኮኖሚ ብዝበዛ፣ሥልጣኑን ለማደላደል በትምክህተኝነት በየማዕዘኑ ከጭቁን ብሔረሰቦች ጋር በአገሪቱ ባሉ ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ጦርነት በመክፈት የሚያደርገው ጭፍጨፋ ኃይልግና ተገዢነት አስጥቶታል::ዛሬ የወታደሩን አምባገነን መንግሥት የሚያገለግለው ኃይል ከየመደቡና ከየሕብረተሰቡ ለግል ጥቅሙ እየፈረሰ የሚመጣ ተባራሪ ግለሰብ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም::

የአምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት የአገዛዝ መሣሪያው የገበዝ ግምጃ አምባገነናዊ ጦርነት ነው::ስለሆነም አገሩ ውስጥ አሉ ለሚባሉ ችግሮች በሙሉ መፍትሔውና መሣሪያው ገበዛዊ አመጽ ነው::

የዛሬው የገዢ መደብ የተመናከረው አዱንሪ የውጭ ኃይሎች በሚሰጡት የጦር መሣሪያና ወታደር እንጂ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ተመርኩዞ አይደለም::እንዲሁም በተቃራኒው ከልዩ ልዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለግል ጥቅማቸው ተመርጠው በተሰበሰቡ ከሲከና በዚህ በውጭ አርዳታ እንጂ፣እምነታቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳልሆነ የመንግሥቱ ዘበኛ 20,000 የኩባ ወታደርና ብዙ ሺህ የምሥራቅ ጀርመንና የሶቭየት የጦር አማካሪዎች ህያው ምስክሮች ናቸው::

በመጨረሻ የወታደሩን መንግሥት ይዘት ገልፀን የመንግሥቱን ዓይነት (State form) ካልገለፅን ሙሉ ገፅን ማየት ስለማንችል <u>የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሥርዓት የመንግሥት ካፒታሊዝም</u> (State Capitalism) <u>ነው እንላለን</u>::<u>የመንግሥቱ የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የሲቪል ሥልጣን የተያዘው በወታደራዊ አምባገነን ትምክህተኛ ኃይል ነው</u>::ይህ ኃይል በመንግሥት አመራር ከክፍለ ሀገር እስከ ርዕሰ ብሔርና ጠቅላላ መሪነት በሁሉም አቅጣጫ ይዟል::ከዚህ ቀደም በአብዮት ስም የተያዙትን እርሻዎች፣ኢንዱስትሪዎች፣ንግዶችን ማለትም ጥቅም ከሥልጣን ጋር ጠብቆ በመያዝ በመንግሥት (State) ሀብትነትም አያገበሰ ኑሮውን ያሻሽልበታል::

ኢሠፓአኮ በሚል አሸነንጊት ድርጅት ስም "ህጋዊ" ሥልጣን ፈጥሮ ንግዱን ለማስፋፋት ጥርጦ ስለተነሳ አምባገነኑ የወታደር መንግሥት የሀገሪቱን ሀብት (ያለችውንም ቢሆን) በሞኖፖል (ለብቻው) ይዞ ለመጋጥ ከውጭ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር ተዋውሏል::

ይህንና ሌሎችን ሁኔታዎች 21ኛው ጠቅላላ ጉባዔ ከመረመረ በኋላ:—

—አምባገነኑ የወታደር መንግሥት የሕዝብ ጥቅም ጠባቂ ሳይሆን የቢሮክራሲውና በተለይም የሶሸየት ተስፋፊ መንግሥት ጥቅም ጠባቂ እንደሆነ ጉባዔው ተገንዝቧል::በዚህም ድርጊቱ አምባገነኑን የወታደር መንግሥት ያወግዛል:: ይታገለዋልም::

—አምባገነኑ መንግሥት ከላይ ከተጠቀሱት ገበሬአበሮች ጋር ሆኖ ፀረ—ዲሞክራቲክ ሥርዓትን በማስፋፋቱና በትምክህተኝነት ተነሳስቶ ብሔረሰቦችን በመጨፍጨፉና የሀገሪቱን ነፃነት ለባዕድ ሀገሮች በመሸጥ ባመጣው ቢሔራዊ ክህደቱ ይህ ጉባዔ ሙሉ በሙሉ ያወግዛል::ለዲሞክራሲ፣ለብሔረሰቦች እኩልነት፣ከሶሸየት ተስፋፊ መንግሥት እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር ተሰልፎ ይህን ኃይል ያለርህራሄ ይዋጋል::

—እስ የመሠረተው ለከሊቦች ጥቅም መጠበቂያ የሆነውን የመንግሥት ከፒታሊዝም ለሕዝብ በሚጠቅም በዕውነተኛ ዲሞክራሲያዊት ሪፓብሊክ ኢትዮጵያ ለመተካት እስከዛሬ ያደረግነውን ትግል አሁንም በቆራጥነት እንደምንቀጥል በዚህ ጉባኤ ቃል ኪዳናችንን እናድሳለን::

- በአጠቃላይ የወታደሩ አምባገነን መንግሥት በማን አለብኝነት ከአቅሙ በላይ ተመጣጣኝ ያልሆነ ውል በመቀዋል የሀገሪቱን ብሔራዊ ክብር በመሸጡ፣
- በትምክህተኝነት ተነሳስቶ ለእኩልነት፣ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ብሔረሰቦችን ያለርህራሄ በመጨፍጨፉ፣
- በፀረ—ዲሞክራቲክነት ተነሳስቶ አገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን የፖለቲካ፣ሕዝባዊ፣ወጣትና ሴቶች ድርጅቶችን ነፃና ዲሞክራሲያዊ ድርጅታቸውን አፈራርሶ በሱ ቡችሎች ለመተካት ሲል የአደረገውን ጭፍጨፋ እሥራትና ስደት በአገሪቱ ላይ በማውረዱ፣

—ከሁሉ በላይ ያለሁ ድርጅት እኔ ብቻ ነኝ በማለት የሌሎች ድርጅቶችን ህልውና በአዋጅ ከነጠቀና "ከገፈፈ" በኋላ ለጭቆና ለዘረፋ ጥርሱን ያገጠጠ፣ ዓይኑን ያፈጠጠ ኢሠፓአኮ የሚል ቅምጥ ጉጅ በመጠፍጠፍ ድሮ "ደርግ" የሚባለውን የፖለቲካ ኃይል ሥልጣን በጉልበት ቀምቶ "<u>በሬትም ያለሁ ወደሬትም የምኖር</u>" የፖለቲካ ድርጅት እኔ ብቻ ነኝ በሚል ኀብዝነት የአገሪቱን አስተዳደር በማተራመሱ 21ኛው ጉባዔ የከፍተኛ መኮንኖችንና የቢሮ ከበርቴዎችን የነሱ ቀና ቀኝ እጅ የሆነውን የሶሸየት ሕብረትና ጭፍሮችን ጭምር በአንድ ላይ ያወግዛል::በዚህ አስተዳደር ምትክ በሕዝብ ላይ እምነት የጣለ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመፍጠር ይታገላል::

3.—<u>በቢሮው ከበርቴ መንግሥት ስለተቋቋሙት ፀረ—ሕዝብ መቀቀሮች ጉዳይ</u>

በአሁኑ ወቅት ፈላጭ ቆራጭ የወታደር መንግሥት ለስሙ ማወደሽ ራሱ ከአቋቋማቸው አድርባይ ድርጅቶች በስተቀር በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዘንድ ምንም ዓይነት ድጋፍ የለውም::

በአብዮታዊው ወቅት (74—76) በሕዝብ ትግልና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ተቋቁመው የነበሩትን ሕዝባዊ ድርጅቶች በማን አለብኝነት እያፈራረሰ እንደገና የፀረ—ዲሞክራሲያዊና ፀረ—ሕዝብ መልክ በመስጠት የመንግሥቱ ተገዢ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ከጀመረ ጥቂት ዓመታት አልፈዋታል::

ምንም እንኳን የአንዳንዶች ድርጅቶች ስም በአብዮቱ አጥቢነት ጊዜ የተሰጠ ቢሆንም ቃሉ በአሁኑ ጊዜ በዚህ ስም የሚነገሩት ድርጅቶችና በተዋቀሮች አብዮታዊ መካከል ምንም



ዓይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ጉባዔው በደንብ ይገነዘባል::

የወታደሩ መንግሥት በሶሸየት ኃይሎች መሣሪያ በኪዩባ ወታደሮችና በምሥራቅ ጀርመን እየተረዳ የአብዮት ቀልበሳ ገና ቢጀምር —ሀ— ብሎ ትግሉን የጀመረው እነዚህ በዲሞክራሲያዊ መንገድ አበበው በማቆጥቆጥ ላይ ባሉ ድርጅቶች ላይ ከፍተኛ ጉሳ በማድረግ ነበር:: ይህም የሆነው እነዚህ ኃይሎች በዚያን ጊዜ በነበረው የኃይል አሰላለፍ ከፍተኛ ቦታ እያገኙ የመጡና ለሥልጣን ተቀናቃኝ (Dual power) ደረጃ የደረሱ ነበሩ::

ከከፍተኛ ቀንከሪያቸው የተነሳ ለምሳሌ ከመጀመሪያ ዙር ጥቃት በኋላ እንኳ አልበገር በማለት ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ያላቸውን እምነት በገሃድ ገልፀው ለዲሞክራሲ እንደሚታገሉና በዚህም ትግላቸው ፅኑ እንደሆኑ በጥቅምት ወር 1977 ዓ.ም መ.ኢ.ሶ.ን ያወጣውን የፖለቲካ ውሳኔ መመልከት ይበቃል::

የወታደሩ መንግሥትና ገበሬ አበሮች እነዚህ የሕዝባዊ ኃይል መሠረት የሆኑት ድርጅቶችን ማጥፋት እንደማይቻል ከተረዱ በኋላ በሆነ ባልሆነ ሰበብ እየወነጀሉ አብዮታዊ መሪዎቻቸውንና (Active) አባላቶን በእሥር ቤት በማጉር፣በመግረፍና በማሰቃየት ከፍተኛ የ ህሳና ወርነት ዘመቻ በማድረግ አባላቶን በማስፈራራት የራባቸውን አድርባይ ጎሰኞች(ስለ ... ቆች)በሥልጣን በማስቀመጥ ሕዝባዊ ድርጅቶችን አኮላሽዋቸው::

በመኢሰማ ውስጥ የማህበሩ መሪዎች በመባል በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡትን አንስተው አንዝባጆችን መረጡ::የገበሬዎቹ የቀበሌ ማህበራት ቅርጻቸው እንዳለ ሆኖ ይዘታቸውን በመቀየር አገር ወዳድና ታጋይ የሆኑትን መሪዎቻቸውን በማጥፋት የአገዛዙ ቀና አውታር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተካሂዷል::

የኢሠፓአኮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ታህሣሥ 20—1972 አዋጅ ከወጣ ጀምሮ እነዚህ ድርጅቶችን በፍጥነት በየስም በየስሙ ደጥሮ የአገዛዝ አውታር ለማድረግ የሚያደርገው ጥድፊያ ሪከርድ ይዟል::በዚህ ባለፉት ዓመታት(72—73) ብቻ ብዙ መስዋዕትነት ባሳየውና በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ስም ባለው ወጣት ሊግ፣<u>ኢሲወማ</u>፣ በጭቆና ሴቶች ስም ለመነገድ <u>ኢሲሴማ</u> በማለትና የከተማና የቀበሌን ማህበራት በልዩ መመሪያ በጥናት ከበዛ እየሸነሸነ፣ድርጅቶችን በአዋጅ እያቀለደ፣እያራበ ለፀረ—ዲሞክራቲክ አገዛዙ መረማመጃ ለማድረግ ዘወትር ቢጥር ይገኛል::<u>አሲተማ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በየፈርጃቸው መደራጀታቸውን አጥብቆ የሚደግፈውን ያህል በስማቸው እንዳይነገድም አጥብቆ ይታገላል</u>::ምንም ዓይነት ዲሞክራሲያዊ ጭንቅላት በሌለበት በፀረ—ዲሞክራሲ አገዛዝ ጥላ ሥር የሚደራጁ ሕዝባዊ ድርጅቶች የመንግሥቱ አገልጋይ ከመሆን አያልፉም::ድርጅቶች ያለ ዲሞክራሲ በአሰት ላይ ያሉ ችግኞች ናቸው::ለጊዜው ይታዩ እንደሆን እንጂ ሥር ስለማይሰዱ ቶሎ ይጠፋሉ::ይከስማሉ:: የድርጅት ሥር የሚያበበው በዲሞክራሲ በሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ብቻ ነው::

እንኳን ልዩ ልዩ ድርጅቶችን ማጠናከር ቀርቶ የሠርቶ አደሩን ፓርቲ አደራጃለሁ ብሎ የተቋቋመው "ኢሠፓአኮ" ወትሮም የወታደሩ መንግሥትና ባዕድ አማካሪዎቻቸው ገበናቸውን ለመሸፈንና በስሙ ለመበዝበዝ ብለው የሠሩት ደባ ስለነበረ ከአምናው ጉባዔአችን ወዲህ እንኳ የነፈሰው ነፋስ ገለባ ገላውን አሳይቶታል::ከርሞ እርቃኑን እንደምናይ አንጠራጠርም::

የዚህ አደረጃጀት ኮሚሽን አባላት ራሱን "ቅብ ቅዱስ" በቀባው ኮሙኒስት (Self babtaized communist) መሪ እየተመረጡ የገቡ የትዕቢተኞች፣የትምክህተኞችና የነፍጠኞች ጉርና ስለሆነ ወዳቂነቱ አያጠራጥርም::ይህ ጉርና ከተቋቋመ ሁለት ጊዜ ተሰብስቦ ውሳኔ ቢያሳልፍም አንድም ጊዜ ሰፊውን ሕዝብ የሚጠቅም ውይይትና ውሳኔ አሳላለፈም::በተለይ ሁለተኛው ስብሰባ በየካቲት 1973 ተካሂዶ አገሪቱ በፖለቲካ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ ምን ያህል ድቀት እንደደረሰባት እንጂ እንደተሻሻለች ምንም ፍንጭ ለራሳቸው እንኳን አጥተዋል::

በዚህ ውይይታቸውና ውሳኔዎቻቸው ላይ ከሕዝቡ ጀርባ የሚካሄደውን በድብቅም በይፋ ዛሬ ስለአለው አንገብጋቢ ችግር ማለትም የረሀቡን ጉዳይ፣የኑሮ ችግሩን ጉዳይ፣የስደተኞችን ጉዳይ አልተነጋገሩም::በዚህም ሥር ተመርኩዘው መፍትሄ ብለው እንኳ ያቀረቡት ነጥቦች ስለሌሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ትዝብት አድርጓታል::ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማስላሉ በዓሳት :—

-21ኛው የአኢተማ ጉባዔ ይህን ኢሠፓአኮ የሚባለውን የውጭ ኃይሎች ቅጥር ድርጅት የአምናውን የፖለቲካ ውሳኔ በመንተራስና ዘንድሮም የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከሚደገፍና ከችገር ከሚያድን መሳዎች ይልቅ ለገዛ ጥቅሙ ሚዛውንና ኃይሉን በማቆሉ በሚያደርገው ድርጊት በሙሉ ፀረ—አንድነት፣ፀረ—ዲሞክራሲ፣ብሔራዊ ክዕደት የተሞላበት በመሆኑ ይህ ጉባዔ ያወግዘዋል፡፡ ይታገለዋልም፡፡

- በዚህ በኢሠፓአኮ ሥር የተደራጁ የሠራተኞች፣የገበሬዎች፣የከተማና የቀበሌ ማህበራት፣የወጣትና የሴቶች የዚህን ፀረ—ዲሞክራሲ ድርጅት ተንኮል በመረዳት፣የወታደሩ መንግሥት የባዕዱ ጥቅም ጠባቂ፣የጦርነት አስፋፊ፣የኢትዮጵያ ሕዝቦች በወንድማማችነትና በመከባበር በመፈቃቀር እንዳይኖሩ እንቅፋትነት፣ችጋር፣በሽታ፣ስደትና አሥርን ያስፋፋ መንግሥት መሆኑን ተረድተው ትግላቸውን ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በማስተባበር እንዲታገሉት ጉባዔው ጥሪውን ያቀርባል፡፡

4:— <u>ብሔራዊ ነፃነትን ስለሚመለከተው</u>

አገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ፊት በነፃነቷ ታኮራ እንደኖረች ይታወቃል፡፡ ስለሕዝቧ የነፃነት ተጋድሎ፣በአፍሪካ ምድር በነፃነቷ ያሰፈትን ክፍለ ዘመናት የቅኝ ገዢዎችን ዱል አያደረገች እዚህ እንደደረሰች ተደጋግሞ ተነግሯል፡፡

ይህን ያህል ዘመናት ነፃነቷን አስከብራ የኖረችው ሀገራችን በጥቂት ለጥቅማቸው በደሩ የከፍተኛ መኮንኖችና የሲቪል ቢሮክራቶች ለሶቭየት ሕብረት ተሸጣለች፡፡ ሶቭየት ሕብረት ገና የአገራችን አብዮት እንደጀመረና የአብዮቱን ሩጥነት፣ሕዝባዊነትና ያሰወሰዱትን እርምጃዎች በየ ጊዜ ይህ ሁኔታ ከምዕራብ ኢምፔሪያሊስት ቁጥጥር ውጭ እንደወጣ ሁሉ በሱ እጅ እንዴት እንደሚገባ፣ከቁጥጥሩ ሥር መግባት እንዳለበትና ከሱ ውጭ ከሆነ ለዓለም ኢምፔሪያሊስት ሀገሮች አደገኛ ምሳሌ እንደሚተው በሚገባ ተረድቶ በዓይነ ቁራኛ ይጠባበቅ ነበር፡፡

በልዩ ልዩ ዘዴዎች ይህን አብዮታዊ ማዕበል ለመከላከል ከሞከረ በኋላ መፍትሄ ያገኘል፡፡ መፍትሄውም በአርባታ ስም ወታደሮች በተለይ በሥልጣን ላይ ያሉትን ለትምህርት ሀገሩ ወስዶ በመመልመልና መልሶ ወደ አገር ቤት በመተካት ከዚያም በአካባቢ ያለውን አለመግባባት አባብሶ ጦርነት ማስነሳት ጊዜያዊ እርምጃው አድርጎ ተጠቀመበት፡፡ ታስቦ የተሰራ እንደመሆኑ መጠን እውነትም ያዘለት፡፡ መጀመሪያ "ሰደድ" ይባል በነበረ አድርባይ ድርጅት ሥር በተሰገሰጉ (pro-Soviet) ሰዎች ስም በጊዜው በነበረው "ኪማሊዳህ" ውስጥ ሁለት አንስተው ሀሜት ፈጥረው አበጣበጡት በዚሁ "አብዮታዊ ሰደድ" ታጅበው አገራቸውን ከሰገቡ በኋላ ለሱ አማካሪ በመሆን፣የሚሆን የማይሆን "መረጃ" እያሉ እየሰጡ ተራማጆችን፣ፀረ—ኢምፔሪያሊስትን፣አገር ወዳዶችን፣ዲሞክራቶችን አስከተቻላቸው አስለቀሙ፡፡ ብዙ ገዳዮቻቸው እያሉ ነፀሁ ኢትዮጵያውያን ተረሸኑ፣ታሠሩ፣ተሰደዱ፡፡ ከዚያም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ጦርነት በማስጫር አካባቢውን ከናወጡ በኋላና አገሪቱን ከሌላ ዓለም ጋር ከአቆራረጡ በኋላ ጦርነት አስነስተው እጅ አገር ከአሠሩ በኋላ ብቻና አርባታ ሰጪ፣ ብቸኛ "ዓለም አቀፋዊ፣ብቸኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሟች" ሆነው ቀረቡ፡፡

ወራት እያለፉ ዓመታት እየተተኩ ሲሄዱ ከ77 ወዲህ በፀረ—አብዮተኛነት የነገሰው አምባገነኑ የወታደር መንግሥት ብሔራዊ ነፃነታችንን በሶቭየት ተስፋፊ መንግሥት በማስደፈር በራሱ ከመተማመን ይልቅ የባዕዱን እጅ እያየ መኖርን እንዲቀበል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሊያስምኑት ሞከሩ፡፡

የወታደሩ መንግሥትና የሶቭየት ኢምፔሪያሊስት በፍፁም በመሃከላቸው የማይጣጣም የጊዜና የተንዛዛ ውል ያውም ለ20 ዓመታት ተዋዋሉ፡፡ ይህ ውል ሙሉ በሙሉ ጠቃሚነቱ ለአዲሱ ኢምፔሪያሊስት ሀገር እንጂ ለኢትዮጵያ ከዕዳ በስተቀር የተረፋት የለም፡፡ ሕዝቡ በሚሊዮን ሲሰደድ፣ሕዝቡ በሚሊዮን በረሀብ ሲያልቅ የሚሰው "ያለ አቻ ጋብቻ" ያመጣበን ጣጣ እንጂ አልል ብሎ የተቀበለው የለም፡፡

አዲሶቹ "ጌቶቻችን" ለኢኮኖሚው ብዝበዛ ያመቻች ዘንድ መሠረቱን የጣሉት በፖለቲካው በመጀመር ነው፡፡



<u>በፖለቲካ</u>፣በኢትዮጵያ ውስጥ ከ74—76 በነበረው ዲሞክራሲ ጭላንጭል በመጠቀም ተቋቁመው <u>በነበሩት</u> የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ከፍተኛ ብጥብጥ በማስነሳት፣የጀመሩትን ቅዱስ ሐሳብ ወደ ተግባር እንዳይለውጡት "በአብዮታዊ ሰደድና" ከውጭ በነበሩት (በልዩ ልዩ ድርጅቶች) ሰላዮች፣የውስጥ አርበኞች በመጠቀም ሕብረቱን አፈረሱት፡፡

ሕብረቱን ካፈረሱ በኋላ በአቋማቸው ፀንተው ትግላቸውን ከሕዝብ ወገን አድርገው በሚታገሉ ድርጅቶች በተለይም በመኢሶንና በኢአወን፣በኢሴዲን . . ላይ ይህ ነው የማይባል (ከውስጥ አርበኞች ጋር በመተባበር) የመግደል፣የማሠር፣የማሰቃየትና የማሰደድ ተግባር ሳይ ሙሉ በሙሉ ተበትኖ በማድረግ ምንም ዓይነት የፖለቲካ ድርጅት ወይም እንቅስቃሴ እንዳይኖር ጣሩ፡፡

ይህን ከሞላ ጎደል ሥራ ላይ ካዋሉ በኋላ (በነሱ ግምት) ደርግ ተብሎ ይታወቅ የነበረውን ሠራዊቱ በየካቲቱ 74 አብዮት ጊዜ መርጦ የላካቸውን ከሚቴ ብትንትኑን በማውጣት ከአጎብዳጆች በስተቀር አገርወዳዶችን፣ተቃዋሚ መስሎ የታየውን ወዘተ አብረው ልዩ ፍጡር ከፈጠሩ በኋላ ኢሠፓአኮ ብለው ስም አወጡለት፡፡ ከርስትና ሲያስነሱት "ደርግ" የነበረ ወደፊትም "የሚናር" ብለው ሰየሙ፡፡

ይህ ቅጥር ድርጅት ከደርግ ሥልጣኑን ቀምቶ የሚቀማለውን የፓርቲ ተግባር ከያዘ በኋላ እንደገና ያለውን ሥልጣን አጠቃሎ ለአንድ ግለሰብ (ለአንድ ብቻና ኮሙኒስት ይሰጣል) የዚህ ሁሉ ሽንገላ አቅጣጫው ግልፅ መሆኑ ለማንም ይገባቃል፡፡ የዚህ ዓይነቱ የሥልጣን በአንድ ሰው እጅ መሆን ለቁጥጥር እንዲመቻች፣ለትዕዛዝ አሰጣጥ ቅልጥፍናን በአጠቃላይ ከብዙ ሰዎች ኃላፊነት የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት ለአዲሱ ኢምፔሪያሊስት ሶቭየት ሕብረትም አመቺ ስለሆነ ነው፡፡

የወደፊት ውጥኑ በዚህ ቅጥር ጉዳ አማካኝነት በሀገሪቱ ውስጥ የሚደረገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በወታደሩ ደንቋ "ከተፈጥሮ ጭምር" በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ነው፡፡ ይህን በማድረግ ሶቭየት ሕብረት በአገራችን "<u>በዓለም አቀፋዊነት</u>" ስም ፈላጭ ቆራጭነትን፣በራስ ከመተማመን በባዕዱ መተማመንን፣ከዲሞክራሲያዊ ውይይቶች ይልቅ ነፍጠኛ፣ትምክህተኛና ትዕቢተኛነትን በሀገራችን እንዲሰፍን አድርጋል ፡፡

<u>የሀገሪቱን ኢኮኖሚ</u> በሚመለከተው ሶቭየት ሕብረት የወታደሩን መንግሥት የአበደ ውሻ ይመስል ጠብ ጫሪ በማድረግ በጎረቤት አገሮችና በየክፍለ ሀገሩ ጦርነት በማስነሳት፣ ከፖለቲካ መፍትሄ የጦርነት መፍትሄ እያስመረጠና እያማከረ ብሔረሰቦችን ከማስጠፋጠፍ አልፎ ትውልዱ የማይከፍለው የጦር መሣሪያ ዕዳ ውስጥ ከተናል፡፡ እሁንም ያለበን የጦር መሣሪያ ዕዳ ብቻ 2.8—3.5 ቢሊዮን ዶላር እንደደረሰ ይነገራል፡፡

በዓለም ገበያ የምናቀርበው ከፍተኛ ሰብል ቡና እንደመሆኑ መጠን በኢትዮጵያ ውስጥ በሌላ የምግብ ጥራጥሬ ምትክ የሰውን ጉልበትና ሀብት (ያለውን Resource) በማንቀሳቀስ አያሌ ሽህ ቶን ቡና እንዲመረት ያደርጋል፡፡ ማንም እንደሚያውቀው ኢትዮጵያ በዓለም የቡና ገበያ የተወሰነ ኮታ (ያውም ትንሽ) ሲኖራት ዋናው ግብ ግን ይህን ቡና ከዓለም ገበያ ዋጋ ባነሰ ወደ ሶቭየትና ወደ ምሥራቅ ጀርመን ለመጫን ነው፡፡ ይህን ቡና እነዚህ አገሮች መልሰው በመሸጥ ብዙ ትርፍ እንዳገኙበት ዓለም ስለሚያውቅ እናልፈዋለን፡፡

አዲሶቹ ኢምፔሪያሊስቶች በዚህ ብቻ አልተወሰኑም፡፡ ከመንግሥት እርሻ" ስም ለም መሬት ከኢትዮጵያ ገበሬዎች እንዲወሰድ በማድረግ ከዚያው ከሚፈራው ጥራጥሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተራበ ለእነሱ ዕዳ እንዲከፍል ይሳካል፡፡ ከስንዴና ከገብስ ወይም ከበቆሎ ወይም ከዚህ ዓይነት የምግብ ጥራጥሬ ይልቅ የዘይት ተክል እንዲተከል ይገፋፋሉ፡፡ ለዕለት ጉርስ ከሚሆን ምርት የበለጠ የሚሸጥ የገበያ ሰብል ( cash crop) እንዲዘራ ያስገድዳሉ፡፡

የሲዳሞን ወርቅና የወለጋውን platinum ማውጣቱንም፣መዘንጉንም፣ማጋዘቱንም እነሱ ስለወሰዱት ሌላ ጣልቃ ገብ የለባቸውም፡፡ በዓለም ከታወቁት የ Potash ክምችቶች ዳናኪል እንዷሉና ከዚህም ቀደም በመጠኑ ይወጣ እንደነበረ ሶቭየቶች ያውቃሉ፡፡ ገን በልዩ ልዩ ምክንያት ተዘግቶ ስለነበረ ምንአልባት እንደ አዶላው ወርቅ በቀርቡ ሳያጠቃልሉት አይቀርም፡፡

ነገሩን በሚመለከት በሶቪየቶች ልዩ ፕሮግራም ስልትና ቅድድር አላቸው፡፡ይኸውም በሀገራቸው ተፈላጊነት የሌለውን ወይም በመከከሳቸው ሾሳን መሠረት ትርፍ ምርት (over-produced)የሆነውን ነገር ከሚገኝ ከተጠለ ለቅኝ አገሮቻቸው ዋጋ ሰያናካፉ ዋጋውን አራብቸው ተመነው በዘቀን አራብቸው አለበው የሚገባበትን ቀንና ጊዜ በደፍር ወስነው ከተፍ ይሳሉ፡፡በዚህ ጊዜ ተቀባይ አገር የተሰጠውን ሰንጠረዥ ፈርሞ "በዓለም አቀፋዊነት" የደረሰበትን እዳ ለመክፈል ቃል መግባት ብቻ ነው፡፡በዚህ ዓይነት የመቶ መኪናዎች ሱቆዎች..ኦበበ ተከምረው ዛሬም ይታያሉ፡፡

: ይህ ነገሩን በሚመለከት ዛሬ በኢትዮጵያና በሶቪየት መካከል ትልቅ ችግር ተነስቷል፡፡ለምሳሌ ያህል በአሜሪካን መሣሪያና ቴክኖሎጂ ተገንብቶ ያደገው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሶቪየት ማመሳለሻ አውሮፕላን እንደቀየረው በደንብ ሲያከናውን በለማቻልና ተበዳሪ በማጣቱ እንደገና በብዙ ችግር ተወጣሬ አንዱ ቦይንግ 727 ከአሜሪካን አገር ለመግዛት በማሰብ ላይ ይገኛል፡፡ከዚህ በተረፈ ሰልቶ ልጉ አገልግሎት በአርዓያ (ከምዕራብ) ሰጪ አገሮች ግፊት(Recomandation) ሃርቨስንዱንስ የተባለ የሩሲያ አውሮፕላን ለመግዛት ተወሰኗል፡፡ይህ ቀጋው አገልግሎቱ በመጠን የሆነ አይሮፕላን አንዱ ከገበ በአገልግሎቱ ከንደሚመደብ በሶቪየቶች ሰለአወቁ ግዢውን ለማስፈፀሚያ ደማይፈነቅሉት ዱጋይ የሉም፡፡ለዚህ የሚከፈለው ልዩ ልዩ የምዕራብ ነሉም አገራዊ ቅኝ ሰዎቹን ሰሰሆነ ለማስቀረት የሚቻል አይመስለም፡፡ገን ግን ያሁኑ በሶቪየት በዚያ ንግድ ተጠቃ አንዱ ወቀት አይሮፕላን አምፕቶ ለመግዛት ቢያስገድደንና ቢያደርጉም ትክክል ነው፡፡የ20 ዓመታት ውለ ቀሰም በይደርቅ መልቀ መልቀ አይቻልምና፡፡

<u>የሚሠበረቀ እሮገ በሚመለከተው፡-</u> ሶቪየት ሕብረት ከገዛ ጎረቤ ጋር አስገልተኛዘ ዱረብ በለማሀበራዊ ኢኮ መሀበበ ትገፋችም ጉዳይ የሰጡም፡፡ትምህርት ቤት በሥራ በቋሠፊ፤የጤና ጣቢያዎች በሰሩቁ በይሰሩቁ፤የውሃ ጉድጓዶ ቢቆፈር በይቆፈር፤ዶክተሮች፤የአቻ ተበበ ሰዎች በበዛ በይበዛ የበነ ቀቅም በአገሪቱ ውስጥ የሚያመናክር አስገልሀነ ዱረበ ንዓቁ አይደለም ፡፡እንደያውም አንዳንዱ ጊዜ በተቃራኒ የነዚህን ኃይሎች መዓበም ይፈልጋል፡፡ለምን? እነዚህ ኃይሎች የፊበን በፊበ መንገል መሠረቶች ናቸውና፡፡ስለዚህ ዛሬ ሶቪየት ሕብረት ሥራ ብሎ የያዘው ዋናበሀል ዘመቻ ወይም የበሀል ለውጥ በማለት በኢትዮጵያ ሕዝቦች አእምሮ ዓይነ ገርዶሽ ቀሉ ለመዝረፍ የሚያደርገው ቀረት ነው፡፡ይህንን በሚመለከት የሚሰጡት መስጠቶች፤የመጡት የትያትር ቡድኖች፤የሚዥረፉት ጋዜጦች በዛታቸው መጠን የለውም፡፡ምንአልባትም በረጅሙ በማሰብ በአገሪቱ ላይ ያሳቸው ቀጥጥር (የ sphere of influence) ቀንካሬ የሚኖረው በዚህ በኩል ቀፉ መሠረት ቢኖረው በመገንዘብ ሊሆንም ይችላል፡፡የኤምፔሪያሊስት የመገቢያ ዘዴ አንዱ ነውና፡፡

ከዚህ በተረፈ ሶቪየት የአገሪቱን ወር መፈነት፤ዓር ቅኅበር አስበባቢነት (በኪዩባ ወታደሮች) መረጃ ሰብሳቢነት (በምሥራቅ ጀርመን) ሁሉ የበላይነትን ይዟል፡፡ለበዙ ዓመት ከ1969 ጀምሮ የሚሠራው የመርከብ ዱክ (floating dack) የአውሮፕላን ጣቢያዎችና የጎዳና ማጠራቀሚያዎች የሄሊኮፕተር ማረፊያዎች እንደሁም ሌሎች አገልግሎቶችን በመሥራት ላይ አገዓሉ የምዕራብ አገሮች መረጃዎች አረጋግጠዋል፡፡ምንአልባት ዛሬ ቢደበቅም ነገ አሜሪካ <u>በርበራ</u> ገበሁ ቢል የሚዘን ጥያቄ ነውና ሶቪየትም <u>ዓህሳቅ</u> ደሴቶች ላይ ነኘ ብሳ ይፋ እንደምታደርገው አንጠራጠርም ፡፡እዚህ ላይ የሁለት ኢምፔሪያሊስት አገሮችን ተገበር ይገልፃል፡፡ትናንት በርበራ ለአሥር ዓመታት የሶቪየት ነበር፡፡ትናንት ያገዉና አከበበው ዓህሳቅ ጭምር የአሜሪካ ነበር፡፡ዛሬ ደግሞ በመሰላቸው ያለችግር በታ ተለዋውጠዋል፡፡

ይህን በመመልከትና ያለፉትን ጉባዔ ውሳኔዎች በመመርመር 21ኛው የአኪቶማ ጉባዔ፡-

- ሶቪየት ሕብረትን እንደ ኢምፔሪያሊስት ሀገር እንደ እንደ ሶሻሊስት አስመቀጠሩን በጥሃቅ ይገልፃል፡፡
- ሶቪየት ሕብረት በዓለም አቀፋዊነት አርዓያ ስም በሀገራችን ጣልቃ በመግባት ፀረ-ዲሞክራቲክ የሆነ ቀምጥ መንግሥት በማስቀመጥና ሙሉ በሙሉ አየረዳ ጭቁን ብሔረሰቦችን በማስጠፍጠፉና በጭፍጨፋው ላይ ተካፋይ በመሆኑ ጎረቤት አገር ወገኖቻችን፤ዲሞክራቶችን፤ተራማጆችን በማስገደሉ፤በማሠሩና፤በማሰደዱ፤እንደሁም ሰብሔራዊ ነፃነትና፤ለዲሞክራሲ፤ለብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮት ትግላችን ሥራ ላይ መዋል በታገሉ ድርጅቶች ላይ ይህ ነው የማይባል ግፍ እንዲደርስ በመተባበሩና በተካሄደና በሚካሄደው ኢሰብአዊ ጭፍጨፋና ጭቆና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመተባበሩ፤
- የሀገራችን ንብረት ያለአግባብ፤ከለተመጣጣኝ ዋጋ በአፃ ከፍያ ስም በመዝረፉ፤በአገረው ሕዝብ ላይ እኔ አውቃለሁ በሚል የትዕቢተኛነትና የዘረኛነት ፖሊሲው፤
- የኢትዮጵያ ሕዝቦች በረሀብ ቢያልቁ አርዓያው ቀርቶ ከአፋቸው በመቀማት ይህ ጉባዔ አጥብቆ ያወግዛል፡፡ይታገለዋልም፡፡

በዚህ ምትክ የገለልተኛ ፖሊሲ አንዲከተሉ፤የተፈጥሮ ወዳጅነት (natural ally) የሚለው ዋጋ እንደሌለው፤ያለአቻ ክብር ቀገኘነትን ከማስከተሉ በስተቀር ሌላ ምንም ዓይነት ጥቅም እንደሌለው በመገንዘብ የአንዱን ሀገር አብዮት መርተው ከገቢው ያስያደሩ ሕዝቦች መሆናቸውን በማመን በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ላይ ጉባዔው አሁንም ወይፈኛም አምነትን ይጥላል፡፡

የወታደራዊ አምባገነን መንግሥት ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ብሔራዊ ነፃነት መገፈፍ መሣሪያ በመሆኑ ከሶቪየት ተስፋፊ መንግሥት ጋር ተባብሮ የኢትዮጵያን ሕዝቦች ለለበደለ በብሔራዊ ሕይወት እናወግዛቸዋለን፡፡

በዚህ መሠረት ጋኪዎቢ፤የሶቪየት ሕብረት፤የምሥራቅ ጀርመንና ግብረአበሮቻቸው ወታደሮች፤አማካሪዎች፤በሳቸው በአስቸኳይ ከአገራችን እንዲወጡ ጉባዔው ይጠይቃል፡፡ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በዓለም ፊት በተቻለው ሁሉ ያጋልጣል፤ይታገላቸዋል፡፡

## <u>የኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግልና የግንባር ጥያቄ</u>

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ከጨሲያን ፋሽስት ወረራ በስተቀር ከውጭ የመጣንለት ወኪኝ፤ከረመኔ፤ፀረ-ሕዝብ አምባገነንና አሸንጉሊት መንግሥት ሥር አስቃቂና አሰፋሪ የሆነ አገዛዝ ተጭኖባቸው የዓቸውን ማየት ከጀመሩ ጥቂት ዓመታት ሆኗል፡፡ይህ ከሃዲና ትምክህተኛ መንግሥት በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ በጠመንጃ አፈሙዝና በዓለም አቀፋዊነት ስም በሚነገረው ተስፋፊ ኃይል አማካኝነት በስልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጦ፤ የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች በበአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በመገፈፍ፤ ግፍ አገዛዝ ከማስቀየቱም በላይ በአሰቃቂ ችግር እንዲኖሩ አድርጓቸዋል፡፡የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ፍትህ፤የዲሞክራሲ መብትንና ብሔራዊ ነፃነትን ለማስከበር የአካሄዱትንና የሚያካሂዱትን መራራ ትግል በማፈን በበዙ መስዋዕትነት የተገኙትን አብዮታዊ ድሎች የልበበ አገሪቱን ታይቶ በማይታወቅ የፖለቲካ፤የኢኮኖሚና የሶሻል ከስረት ውስጥ ከቷታል፡፡በተካሄደው የቀልበሳ ሤራ፤ተያይዘው በመጡት ልዩ ልዩ ጭቆናዎችና በአገሪቱ ላይ በደረሰው ኪሳራት፤ሥልጣን የቀቀማቸው ማስጠበቂያ ካደረጉ አንዳንዱ ከፍተኛ የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራቶች በስተቀር ያልተነካ/ያልተበደለ ህብረተሰብ ክፍል አይገኝም፡፡

በሥልጣን ላይ ተደላድሎ ለመቆየት በሚያካሂደው ጭፍንና የትምክህተኛነት ጭፍጨፋ ልጅ የሞተበት፤አባት የሞተበት፤እናት የሞተበት፤እህት የሞተበት፤ጓደኛ የሞተበት፤በአጥፍ ዱርብ ደግሞ የታሰረበትና የተሰደደበት ሰው በሀገሪቱ ውስጥ ስፍር ቁጥር የለውም፡፡

ይህ ትምክህተኛና አምባገነን መንግሥት፤በተለይም ከመጋቢት 1969 ዓ.ም ጀምሮ አምነቱን በተስፋፊ የውጭ ኃይል ትከሻ ላይ ከጣለ በኋላ፤ጭቁን ሕዝቦች በከፍተኛ መስዋዕትነት በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ላይ የተቀዳጁትን ድሎች በማከሸፍ ለዲሞክራሲና ለነፃነት በሚታገሉ ኃይሎች ላይ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ በማካሄድና በአሥር ቤት አጉሮ በማሰቃየት፤ከኃይለ ሥላሴ መንግሥት የባሰ የአረመኔ አገዛዝ አስፋፍቷል፡፡በዚህ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ ለብሔራዊ ነፃነት፤ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መመስረት ለሕዝብ ብልጽግና ቢታገሉ የቆዩ አያሌ ወ

ዝአደሮች፣አርሶአደሮች፣የሴቶች ታጋዮች፣የብሔረሰብ ታጋዮች እንዲሁም አገሪቱ በአጭር ጊዜ ልትተካቸው የማትችለው ምሁሮች ሕይወታቸውን አጥተዋል።በዚህ ወደር በሌለው ጭቆና የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የመናገር የመፃፍና የመደራጀት መብታቸው መገፈፍ ብቻ ሳይሆን፣ዘረኛው የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በጥቁር ሕዝቦች ላይ እንደሚያደርገው ጭቆና ዓይነት፣የመንቀሳቀስ መብታቸውን ተገፈው በትውልድ አገራቸው የቁም እሥረኞች እንዲሆኑ ተገደዋል።ሰፊው ሕዝብ በከፍተኛ መስዋዕትነት ያቋቋማቸው ሕዝባዊ ድርጅቶችና መሪዎቻቸው ተረሽነው፣ግማሾች ሲፈራርሱ ግማሾች ደግሞ ፀረ—ሕዝብ ተሹሞ በላያቸው ላይ እየተቀመጠ ራሱን ሕዝቡን መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች እንዲሆኑ ተገደዋል።ይኸው አምባገነን ወታደራዊ መንግሥት በሚያካሂደው ትምክህተኛ ፖለቲካ፣ጭቁን ብሔረሰቦችን ከኃይለ ሥላሴና ከምኒሊክ ዘመን በበለጠ አረመኔነት በተሞላበት ዘዴ ይጨፈጨፋሉ።ይህ ጭፍን ጭፍጨፋ በወንድማማች ሕዝቦች መካከል ለትውልድ ሊቀረስ የሚችል ደም መቃባትን ከማስከተሉም በላይ በሀገሪቱ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ትምክህተኝነት ከዳር እስከ ዳር እንዲስፋፋ አድርጓል።በአሁኑ ወቅት በምሥራቅ፣በምዕራብ፣በሰሜን፣በደቡብ የዚህ የትምክህተኛ መንግሥት ጥይት የማያፈጭበት አንድም አከባቢና ጭቁን ሕዝብ አይገኝም።ለዚህ በጭቁን ሕዝቦች ላይ የሚካሄድ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ትምክህተኛው የወታደር መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ተስፋፊ የሶቭየት ሕብረት መንግሥትም በቀጥታ በታሪክ ፊት ተጠያቂ ነው።

የሶቭየት ሕብረት ያሻንጉሊቱን መንግሥት በስልጣን ላይ ለማቆየት ብቻ ሳይሆን፣በሀገሪቱ ውስጥ ሰፊው ሕዝብ ጉልበቱን አፍስሶ የሚያመርተውን ካፒታል የሚዘርፍበት አንደኛውና ዋናው መንገድ ከጦር መሣሪያ ሽያጭ ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣የሰፊው ሕዝብ ደም በከንቱ እንዲፈስና ጦርነቱ እንዲፋፋም፣እንዲስፋፋ ጥብቅ ፍላጎት አለው።

ሶቭየት ሕብረት የጦር መሣሪያ በብዛትና ያለማቋረጥ ወደ ሀገሪቱ ማስገባት የሚችለው ትምክህተኛው መንግሥት በጭቁን ብሔረሰቦች ላይ ጭፍጨፋን ሲያካሂድና ጦርነቱ ሲፋፋም እንደመሆኑ መጠን፣በብሔረሰቦች ላይ የሚደረገው ጭቆና እንዲፋፋምና በሰፊው ሕዝብ መካከል ያለው መለስተኛ ቅራኔዎች እንዲከረሩ ያለማቋረጥ ይጥራል፣ ተንኮሉም ይሸርባል።አሻንጉሊቱ የወታደር መንግሥትም የኃያል መንግሥት ክንዱ በመደገፍ ሥልጣን ላይ ተቀምጦ ለመቆየት ካለው ፍላጎት የተነሳ፣በውጭም በውስጥም የሚከተለው ፖለቲካ፣የዚህን የተስፋፊ መንግሥት ጥቅም ለመጠበቅ ቆርጦ የተነሳ መሆኑ በግልፅ ይታያል።

ዛሬ ሀገሪቱ ያለችበትን የኢኮኖሚ ሁኔታ ብንመለከት በገጠርም ሆነ በከተማ የነበሩ የኢኮኖሚ ተቋሞች እንኳንስ ሊያድጉ ቀርቶ፣ከነጭራሹ እንዳልነበሩ በመሆን እየወደሙ ናቸው።በገጠር የመሬት አዋጁ ሥራ ላይ ባለመዋሉ፣ጭቁን ገበሬዎች የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብቶቻቸውን በመገፈፋቸው፣የመሬትን አዋጅ በተግባር ለመተርጎም እንዲያገለግሏቸው ያቋቋሟቸው የገበሬ ማህበራት በመፈራረሳቸው፣በዲሞክራሲያዊ መንገድ የመረጧቸው ተወካዮች እየተለቀሙ በመታሠራቸውና በመረሸናቸው፣የብሔረሰቦች ጭቆናና ጭፍጨፋ በመፋፋሙ፣ጭቁን ገበሬዎች በሚያመርቱት ትርፍ ምርት በለውጡ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጉ ቀላል የኢንዱስትሪ ምርቶች፣በቂ ሸቀጦች ሊያገኙ ባለመቻላቸው፣በአገሪቱ ውስጥ የሚመረተው ሀብት ምርትን ለማሳደግ በይውል ለመሣሪያ መግዣና ጭቁን አርሶ አደሮችን ለመጨፍጨፊያ ስለሚውል፣ገበሬው በሰላም እንዳያመርት በየጊዜው የቦንብ ናዳ ስለሚወርድበት፣መሬቱን እየተወ በየሥፍራው የሚሸሸው ጭቁን ገበሬ እንኳንስ ምርቱን ሊያሳድግና እንደልቡ ገበያ ለማውጣት ቀርቶ ለራሱ የዕለት ጉርሱን ለማምረት አልቻለም።በየከተማውና በየገጠሩ እህል ጠፍቶ እረሀብ መስፋፋቱ ለዚህ ቋሚ ምስክር ነው።

በከተማም እንደዚሁ በወዛደሩ ላይ በሚደረገው አመፅ፣በዲሞክራሲ መጥፋት፣እንዱስትሪ ለማስፋፋት መዋል የሚገባው ሀብት ለሕዝብ መጨፍጨፊያ ለሚሆን መሣሪያ መግዣ በመዋሉ፣ያሉትም አስተዳደራቸው (industrial managements) በገዱ የለሽ ቢሮክራሲ ቁጥጥር ሥር በመዋላቸውና ምስቅልቅላቸው በመውጣቱ፣ለምርት የሚያስፈልጉ ጥሬ እቃዎች (raw materials) በቀላሉ ባለመገኘታቸው፣የመሣሪያ መለዋወጫ እንደልብ ባለመገኘቱ፣ወዝአደሩ ከምርት ላይ እየተነሳ ከፊሉ እሥር ቤት ሲታጐር ከፊሉ ደግሞ በገዛ ወገኑ ላይ እንዲዘምት በመደረጉ፣የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማሳደግ በፍጹም አልተቻለም።



በሶሻልም በኩል ያለውን ሁኔታ ብንመለከት ከዚህ የጠለቀ ነው።ዛሬ አምባገነኑ መንግሥት በፈጠረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ የሥራ አጡ ቁጥር፣የሴትኛ አዳሪው ቁጥር እየጨመረ ሄዷል።እርሀብ የጠቀሳሰው ሕዝብ የዕለት ተዕለት ኑሮ ዓይነተኛ መለያ ሆኗል።

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተዘረዘሩት ምክንያቶች ዛሬ በአገሪቱ ውስጥ ያልተማረረና ያልተቆጣ፣በየቦታው የመሣሪያና የፖለቲካ ትግል የማያካሂድ ሕዝብ የለም።

ጭቁን ብሔረሰቦች የሚካሄዱባቸውን ጭፍጨፋ ለመቋቋም በምሥራቅ፣በምዕራብ፣በሰሜን፣በደቡብ፣በየስፍራው የመሣሪያና የፖለቲካ ትግል ያካሂዳሉ።በሰሜን የኤርትራና የትግሬ ሕዝቦች፣በደቡብ የኦሮሞ ሕዝብ፣በምሥራቅ የኦጋዴን ሕዝብና እንዲሁም ሌሎች ጭቁኖች የመሣሪያ ትግል በማካሄድ ላይ ናቸው።

ምንም እንኳን ዛሬ በአገሪቱ ውስጥ በተስፋፋው ትምክህተኝነትና በብሔረሰቦች ላይ በሚደረገው ጭቆና ምክንያት የብሔረሰቦች ትግል ከሁሉም በበለጠ ቢጋጋልም፣ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎችም አምባገነኑን የወታደር መንግሥት ለመቋቋም የሚያካሂዱት ትግል በቀላሉ የሚገመት አይደለም።ወዝአደሩ፣አርሶ አደሩ፣ጭቁን ሴቶች፣ጭቁን መለዮ ለባሹ፣አገር ወዳድ ምሁራኖች፣ወጣቶች፣ዝቅተኛ የቢሮ ሠራተኞች በተለያየ መንገድ በየአለበት ትግላቸውን ያካሂዳሉ።

ይህ በተለያየ ዘዴና በልዩ ልዩ ሥፍራ ከአምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት ጭቆና ለመላቀቅና በዲሞክራሲ፣በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ኑሮ ለመገንባት በየሕብረተሰብ ክፍሉ በተናጠል የሚካሄደው ትግል ወደ ዳር እንዲያመራ በትክክለኛ የፖለቲካ መሥመር ላይ ተመሥርቶ መቀናበር አለበት።ለዚህ ግብ ማለትም የተቀነባበረ የሕዝቦች ትግል ወደ ዳር እንዲያመራ፣ብሔራዊ ነፃነት እንዲከበር የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ብዙ አባላቱን በትግል ሜዳ አሰማርቶ መስዋዕት በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል።በማድረግ ላይም ይገኛል።ምንም እንኳን በአለፉት ሦስት አመታት ውስጥ በዚህ ድርጅት ላይ አምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥትና ግብረ አበሮቹ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ቢያካሂዱበትም፣ከቆመበት የፖለቲካ መሥመር ባይዘነፍ ለዲሞክራሲ፣ለእኩልነት፣ለብሔራዊ ነፃነት፣ለተራማጆች ሕብረት ወዘተ ያለማቋረጥ እየታገለ ነው።

በወጣቱም በኩል የሚደረገውን ትግል ትክክለኛ ፈር ለማስያዝና በጠቅላላ ወጣቱን አስተባብሮ የሚካሄደውን የትምክህተኞችና የአምባገነኖች ዓመጽ ለመቋቋም የኢትዮጵያ ወጣቶች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢ አ ወ ን) ያደረገውና የሚያደርገው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው።ይህ ድርጅት ለዲሞክራቲክ አብዮት፣ለብሔረሰቦች እኩልነት፣ለብሔራዊ ነፃነት፣ለአብዮታውያን ሕብረት፣ለሕዝብ ብልጽግና ወዘተ ስለታገለና ስለሚታገል በአምባገነኑ መንግሥትና በግብረ አበሮቹ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ተካሂዶበታል።ከዚህ ጭፍጨፋ በተረፈ ኃይሉ አሁንም ያለ አንዳች ፖለቲካዊ ማፈግፈግ በመታገል ላይ ይገኛል።

እንዲሁም በሴቶች አካባቢ፣የጭቁን ሴቶችን ብሶት በማንሳትና ትግላቸውን በማስተባበር፣ጭቁን ሴቶች ከድርብ ጭቆና ተላቅቀው በእኩልነት እንዲኖሩና በሕብረተሰቡ የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የሶሻል እድገትና ግንባታ ውስጥ ተገቢ ቦታ እንዲኖራቸው የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ (ኢ ሴ አ ን) ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክታለች።ለዚህ አብዮታዊ ተግባር በመበርከቷም በአምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት ጭፍጨፋ ተካሂዶባታል።ይሁንና ይህ ጭፍጨፋ ከትግል ሜዳ አደናቅፍ ባያስጠፋት ዛሬም ለዲሞክራሲ፣ለእኩልነት፣ለብሔራዊ ነፃነት በመታገል ላይ ትገኛለች።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ሰፊው ሕዝብ፣የሚካሄድበትን አመጽ ለመቋቋም፣ከዳር እስከ ዳር መነሳቱን እናያለን።ሆኖም ይህ ትግል ያልተቀነባበረ፣ተናጠል በመሆኑ፣አምባገነኑን መንግሥትና ግብረ አበሮችን ለመጣል አላስቻለም።ይኸ ከሃዲ አሻንጉሊት መንግሥትና ግብረ አበሮቹ የተባበረ ሕዝብ ክንድ ሳይደቁሳቸው በተናጠል ትግል የሚበገሩ ባለመሆናቸው፣ዛሬ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ይህን ተበታትኖ የሚገኘውን የሕዝብ ትግል ማስተባበርና የጋራ ጠላትን በአንድነት ክንድ እንደመታ ማድረግ ነው።

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 21ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ከላይ የተዘረዘሩትን

ሁኔታዎች ከመረመረ በኋላ የሚከተሉትን ውሳኔዎች አሳልፏል:-

1) በተለያዩ ቦታዎች የሚካሄዱት የጭቁን ብሔረሰቦችን ትግል እየደገፈ፣ ለብሔረሰቦች እኩልነትና የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን ለማስከበር በሚደረገው ትግል ከጎናቸው ተሰልፎ ይታገላል::

2) ያልተደራጁ የሕብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ አምባገነኑን ወታደራዊ መንግሥትና ገብረ አበሮችን ለመጣል በሚደረገው ትግል ውስጥ ተገቢ ቦታቸውን እንዲይዙ ጥሪ ያደርጋል::

3) ማህበራችን በተደጋጋሚ ለመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ፣ለኢትዮጵያ ወጣቶች አብዮታዊ ንቅናቄ፣ለኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ የሰጠውን ድጋፍ እንደገና በማደስ፣አምባገነኑ በእነዚህ ድርጅቶች ላይ የሚያደርገውን ጭፍጨፋና እሥራት ያወግዛል::እነዚህም ድርጅቶች ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ጥሪ ያቀርባል::ከዚህም አያይዞ "የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ"ከሌሎች ተራማጅ ኃይሎች ጋር፣ከብሔረሰቦች ታጋዮች ጋር የትግል ትብብር ለማድረግ የሚያካሂደውን ጥረት እየደገፈ፣በዚሁ ጥረት እንዲገፋበት ጥሪ ያቀርባል::

4) ለብሔራዊ ነፃነት፣ለዲሞክራሲ፣ለፍትህ፣ለብሔረሰቦች እኩልነትና የራስን እድል በራስ ለመወሰን በየአቅጣጫውና በየቦታው የሚደረጉት ትግሎች ዘላቂ ፍሬ ሊሰጡት በሰፊ የጋራ ትግል ግንባር በአንድነት ሲቀናበሩና የወታደሩን መንግሥት ከነገብረ አበሮቹ ሲደመስሱ ብቻ ስለሆነ፣ለዚሁ ሰፊ የጋራ ግንባር መመሥረት ማህበራችን ደጋግሞ ያቀረበውን ጥሪ በማደስ፣በዚህ አገባር ለሚደረገው ትግል ማህበራችን በተቻለው አቅሙ አስተዋጽዖ ለማድረግ እንደሚጥርና እየጣረ እንደሆነ ያስታውቃል::

6)- <u>የኢኮኖሚንና የማህበራዊ ጉዳይ ስለሚመለከተው</u>

የወታደሩ አምባገነን መንግሥትና ተስፋፊው የሶቭየት ሕብረት መንግሥት ተባብረው ሀገሪቱን በይፋ እጃቸው ካስገቡበት 1977 አንስቶ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት ውስጥ ከተቀታል::

<u>እርሻን ስንመለከት</u>፣ወታደሩ አሁንም የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ለእርሻ ነው ብሎ አሥር ጊዜ ቢምልም በዚህ በኩል አልተሳካም::እንኳንስ ተሻሽሎ ለመገኘት ድሮ የነበረበት ደረጃ ለመድረስ አልቻለም::በመንግሥቱ በራሱ ሪፖርት ከሀገሪቱ <u>ለም መሬት</u> 78,000,000 ሄክታር ( 65 ከመቶ) መሬት የታረሰው 10 ከመቶ ብቻ ነው::ከ74 በፊት የጥራጥሬ ምርት 5.0 ሚሊዮን ቶን በዓመት ቢሆን አሁን ያንን ያህል ለማምረት እንኳ አልተቻለም::በዚያው መጠን ምግብ ፈላጊው ሕዝብ 2.5 በመቶ በዓመት ያድጋል::ድሮ ጥራጥሬ ለንግድ ማቅረብ ቢቻል ዛሬ እንኳን ለንግድ ለዕለት ምግብ ስለጠፋ ወደሸማችነት ደረጃ ወርደናል:: ከ1976—1977 ብቻ 130,000 ቶን በላይ ሀገሪቱ በውጭ ዋጋ ጥራጥሬ ሸምታለች፣(ይህ ከእርዳታ ውጭ ነው::) በ1977 ብቻ 172000 ቶን ተሸምቷል::በነዚህ ዓመታት በደረሰው ረሀብ አሁን ስንት ሚሊዮን ቶን ጥራጥሬ እንደሚያስፈልግ ለመገመት እንኳ ያስቸግራል::

ምንም እንኳ በሀገሪቱ ላይ የተፈጥሮ ችግሮች እንደ ዝናብ ማጣት ያሉ ሁኔታዎች ሁኔታውን ቢያባብሱም ለዚህ ዋና ተጠያቂው የወታደሩ መንግሥትና ገብረ አበሮቹ ናቸው:: ረሀብ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚመጣ ቀደም ብሎ ለደርግ በቀረበው ሪፖርት ይህ ሁሉ ችግር በዝርዝር ቀርቦ የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ በማለት ተወው::ከዚያም በሥልጣን ላይ በቆየበት ዘመን እጅግ ወደ ኋላ የቀረውን የእርባታ ኃይል እንኳ ለመቀየር ባይችል ለማሻሻል እንኳን ባለመሞከሩ ያለው የርባታ ኃይልና ዘዴ ካለው የሕዝብ ቁጥር እድገት ጋር በፍጹም ሊመጣጠን አልቻለም::

በአንድ ቦታ በተለይ ቡና በሚበቅልበት አካባቢ ለቡና ምርት ከፍተኛ mobilization ቢደረግም ከዚህ የሚገባው ገንዘብ እንዳለ ለጦር መሣሪያ እዳ ስለሚከፈል ተ



ጠያቂው ሕዝብ ሳይሆን የሶቭየት መንግሥት ነው::አንዳንድ ጎበዝ ገበሬዎች ከምግባቸው አትርፈው ለገበያ በሚያመርቱበት ወቅት ሀብታሞች ሆናችሁ እየተባሉ ስለሚጠቁና ሰው ቦታቸው ለመንግሥት እርሻ ተወርሶ ለ cashcrop ስለሚሆን፣የመንግሥት እርሻ ምርት እንዳለ ለውጭ ምንዛሬ ከዚያም ለእዳ ስለሚሄድ አገሪቱ እያደር እየቆረቆዘች ሄደች::የመንግሥት እርሻም የተባለው ዋናውን ትኩረት የተሰጠው ለ cash crop ስለሆነ በዘመናዊ መሣሪያ የሚታረሱት የምግብ ሳይሆኑ የገበያ እህሎች ብቻ ሆነዋል::ይህ የመንግሥት እርሻ የብር ከበርቴው ጥቅም ምንጭ ነው::ያለ መንግሥት እርሻ የከበርቴ መንግሥት የለምና ዛሬ ወታደሩም ዓይኑን የጣለው በዚህ ላይ ነው::ለምሳሌ በየካቲት/73 በሁለተኛው ኢሠፓአኮ መደበኛ ስብሰባ ላይ በቀረበው ሪፖርት የመንግሥት እርሻና የገበያ እህል ምን ያህል እንደጨመረ ለመግለጽ "የመንግሥት እርሻ"ቦታ አዋጅ ከወጣ እስከ 79 ድረስ 73000 ሄክታር ብቻ ቢሆን በ79/80 ግን 330000 ሄክታር ለም ቦታ ደርሷል ይላል::ምንም እንኳ የእርሻው መስፋፋት ተገቢ ቢሆንም መንግሥት ይህን ቦታ ጠፍ በማልማት ሳይሆን የለማውን በመቀማት ስለሆነ ችግር ያባበሰ እንጂ መፍትሄ ሊሆን አይችልም::

የደን ሀብትን በሚመለከተው በኩል ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ 16 ከመቶ የሸፈነው ደን ዛሬ 4 ከመቶ ብቻ ቀርቷል::የከተማውና የገጠር ሕዝብ ማገዶ እንጨት እስኪተጠቀም ድረስ በዚሁ ስለሚቀጥል በ10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሀገሪቱ ምንም ደን እንደማይኖራት ይገመታል::የደን መጥፋት የአየር መጥፋትን ያስከትላል::የአየር መበላሸት ዝናም ይከሰክሳል::ድርቅ ያመጣል::ማገዶ ብቻ ሳይሆን ብዙ ገጠሽ በመጠቀም አየሩ ተበላሽቷል::ሣሩ ደርቋል::ይህን አሳሳቢ ሁኔታ ለመወጣት ግን ምንም የተወሰደ እርምጃ የለም::

ሀገሪቱ በጋማና ቀንድ ከብት ሀብታም አገር ብትሆንም በድርቅ ብዙው ሞቷል::ድርቅ በደረሰባቸው አገሮች የሚገኙ የጋማና የቀንድ ከብቶች3/4ሞቷል::አሁንም እነዚህን የጋማና የቀንድ ከብት በደንብ ይዞ ለሰፊው ሕዝብ በሚሆን ዓይነት ምግብ ለመሥራት የሀገሪቱ እንዱስትሪ ችሎታ ስለማይፈቅድለት ገበሬው ከብቱን እስኪሞት እንደሰው ከመቅበር ሌላ ሊጠቀምበት አልቻለም::

<u>እንዱስትሪን ብንወስድ</u>፣ድሮም ቢሆን ሀገሪቱ ያላት ትንሽ እንዱስትሪ ነው::መቼም ጊዜ ቢሆን የሕዝቡን የመግዛት ፍላጎት አሟልቶ አያውቅም::ያለችን ትንሽ እርሻ እንኳ ወደ እንዱስትሪ ምርት መለወጥ አልተቻለም::በሀገራችን ካሉት ጥቂት እንዱስትሪዎች እንኳ በሰበብ በአስባቡ የሚዘጉ በመቀያየሪያ ጥፋት የቆሙ ብዙ ናቸው::በንግድም ሆነ በሠራተኛ ብዛት ቀቅማቸው ትንሽ ነው::ለምሳሌ በእርሻው ዘርፍ ከ90 በመቶ የገጠር ነዋሪ 80 ከመቶ ሥራ ቢሰጥ ለምሳሌ ቡና ተከልና ለቀማ 7 ሚሊዮን ሠራተኞች ቢይዝ ከ10 በላይ የሆኑት ጥቃቅን እንዱስትሪዎች የያዙት ሠራተኛ ብዛት 69000 ያህል ብቻ ነው::በንግድ በኩል ከፍተኛ ገቢ አሁንም ከእርሻው እንጂ ከእንዱስትሪ አይደለም::ከውጭ ንግድ ሦስት አራተኛው (export) የሚይዘው ቡና ቢሆን የእንዱስትሪ ምርቶችን ብንወስድ 35 ከመቶ በታች ናቸው::

ጨርቃ ጨርቅ 20 ከመቶ ንግድ export ያደርጋል::
ቢራ 10 ከመቶ ንግድ export ያደርጋል::

የቀረው ከትንባሆ፣ከቆዳ (ከፍተኛው)፣ከእንጨት፣ከዘይት ምርት ይሆናል::በሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ጥቃቅን እንዱስትሪዎች እንዱ ሦስተኛው የተያዘው በአሁኑ የወታደር መንግሥት ነው::ይህ ማለት ከእንዱስትሪ ውጤት 90 ከመቶው የሚገባው ለወታደሩ መንግሥት ቢሆን በዚህ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከሚተዳደሩ ወዝአደሮች ሠራተኞች 80 ከመቶውን የያዘ ነው::

እንደ ትጉዎች ገበሬዎች ሁሉ ትጉ የእጅ ጥበብ አዋቂ አስፋፍቶ ለመሥራት ታጥቆ የተነሳ በሙሉ በከበርቴነት ተወንጅሎ ንብረቱን ይቀማል::አገሪቱ ባለችበት በአሁኑ ደረጃ ትንንሽ የቤትና የጎጆ እንዱስትሪዎችን፣ትንንሽ እርሻዎች እንዲያብቡና ምርት ለገበያ እንዲያቀርቡ ከመገፋፋት ይልቅ የወታደሩና የሶቭየት ሕብረት ካድሬዎች "በመንግሥት ምርጫ" ስም አደቀባቸውን እንዳያስፋፉና በመፍጠር ችሎታቸው እንዳይጠቀሙ ይጠቀፏቸዋል::

<u>የማዕድን ንግድ በሚመለከተው:-</u>
በሲዳሞ ወርቅ 250 ኪ.ግራም በዓመት፣በወለጋ 52 ኪ.ግራም በዓመት ሶቭየት እራሱ እያወጣ ይወስዳል::

— በዓመት 157 ሚሊዮን ቶን potash ከዳንከል ቢገኝም ለጊዜው ተዘግቷል።
— ከአድግራ በቻጋን የሚወጣው copper ከ76 ጀምሮ ተዘግቷል።በአጠቃላይ ሶ ቭየት ከሚወስደው በስተቀር የማዕድን ንግድ በአገራችን ቆሟል ማለት ነው።

ንግድን በንመለከት፦ የወታደሩ መንግሥት በንግድ በኩል ያመዘነው ወደ ምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ቢመስልም አሁንም ቢሆን ዋና ንግዱ ከምዕራብ አገሮች ጋር ነው።ነገ ከ ገራችን አሁን ያለው ንግድና በፊት የነበረው ይለያል።አሁን የምንሸጠው ለምሥራቅ አገሮ ች ቢያደላ፤ከጦር መሣሪያ በስተቀር የምንገዛው አብዛኛው ከምዕራብ ነው።ከምዕራብ አገሮ ች የምንገዛው (import) 80 ከመቶ ሲጠጋ እና የምንሸጥላቸው (export) 20 ከመቶ፤ለአንዳንድ አገሮች ደግሞ ከ50—100 ከመቶ ቀንሷል።በዚህም ምክንያት የወጭ ም ንዛሬ ችግር አምጥቶብናል።

የቡናን ንግድ በሚመለከት፦ በዓለም የቡና ገበያ (International coffee organ. (I.C.O.) ውስጥ የቡና ሽያጭ ኮታ 36000 ቶን ሲሆን፤በ1980 ጀርመ 87000 ቶን ምርት ተገኝቶ ከዚህ I.C.O. ኮታ የተረፈው ለሶቭየትና ለምሥራቅ ጀርመ ን በርካሽ ተሸጧል።ዘንድሮ ከ100,000 ያላነሰ ለማምረት እቅድ አለ።ይህ ዓላማ ከተ ሳካ፤ለሶቭየትና ለምሥራቅ ጀርመን ቶን ሲወጣ፤የቡና ዋጋ 40 ከመቶ በመቀነሱ ለኢትዮጵያ ገበሬ የባሰ ጭንቅ ይጠብቀዋል።

በ80/81 የቆዳ ዋጋ ስለቀነሰ በዚህም በኩል ያለው ሁኔታ ችግሩን አባብሷል። እንደ ማንኛውም ንግድ በቡናና በቆዳ ንግድ የተሰማራው የወታደሩ መንግሥት ነው።በመ ንግሥቱ ሪፖርት መሠረት በቡና፤በቆዳ ንግድ የመንግሥት ድርሻ 65 ከመቶ እንደደረሰና በ ቅርቡ ቡና እንደሚል ተነግሯል።የመንግሥት የንግድ እርሻ (Government marketing Co-operative) ቡና የመግዛት ድርሻው በሁለት እጅ ሲጠጋ ግለሰብ የቡና ነ ጋዴዎች ቡና ለመግዛት ገደብ ተደርጎባቸዋል።በመጀመሪያ ነጋዴ የንግድ ፈቃድ ማውጣት አ ለበት (በጣም አስቸጋሪ ፈተና) ከዚያ በኋላ ቡና ለመግዛት የሚችለው በጨረታ ሲሆን፤የመ ንግሥት ንግድ ድርሻ ግን ያለ ጨረታ፤በቀጥታ ከገበሬው ላይ እራሱ በወሰነው ዋጋ ይገዛል።

የሽያጭ (export) ንግዳችን ይህን ሲመስል የገዢ (Import) ንግዳችን ከ ዚህ የተለየ በሩህ መልክ የለውም።በአለፉት ዓመታት ውስጥ ከውጭ ሽያጭ (export) የውጭ ገዢ (Import) ያለልክ በልጧል።የምንገዛቸው ዋና ዋናዎቹ የፍጆታ እቃዎች (consumption goods) ሲሆኑ፤በተለይ ነዳጅ ከሽያጭ ገቢያችን 70 ከመቶውን ይ ወስዳል።

በ1980 ዓም የዓመቱን የመጀመሪያ ዓሻ ብቻ እንኳ ብንመለከት የሚከተለውን እ ናያለን፦

የውጭ ሺያጭ (Export) $263·9 ሚሊዮን
የውጭ ገዢ (Import) $318·0 ሚሊዮን
ግዛን $54·1 ሚሊዮን

በልዩ ልዩ አቀጣጦች ያለብንን ዕዳዎች ስንመረምር:—
በንግድ ሚዛን መዛባት $109·8ሚሊዮን
የበጀት ጉድለት ብድር $1411·4 ሚሊዮን
ከእነዚህ እዳዎች ሌላ ለሶቭየት ሕብረት የጦር መሣሪያውን ለአሻንጉሊቱ መንግሥት እያስታቀ ፈ ከ$2·8 እስከ $3·5 ቢሊዮን የሚደርስ እዳ ቀልብናል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ያለችበት የኢኮኖሚ ቀውስ በየትኛውም አቀጣጫ ቢያዩት ጎልህ ሆኖ ይታያል።የዓለም ኤክስፐርቶች እንደሚሉት ኢትዮጵያ ያላት ሪዘርቭ ለስምንት ሳምንት የሚበ ቃ ብቻ ነው።

የትምህርት፤የጤና፤የመገናኛ ወዘተ ችግሮች ከኢኮኖሚ ጋር የተያያዙ ስለሆኑ የሚገ ኙበትን ሁኔታ በቀላሉ መገመት ይቻላል።የአስተማሪ ችግር አሁንም በጣም ጎልህ ነው።በ ጤና በኩል እንደ ዶክተሩ አሁንም 200 አልጋ ለ100,000 ፎሬ፤አንድ ሐኪም ለ100,000 ፎሬ ነው።ከሚወለደው ሕፃናት ዓመት ሳይሞላው የሚሞተው ከ51 ከመቶ በላይ ነው።እያን ዳንዱን ችግር እንነሳ በዝርዝር ለማሳየት በምክር አውሉ ከማስደር አልፍ ያከርማል።በአ



ጠቃላይ አገሪቱ የገባችበት የፖለቲካ፤የኢኮኖሚና የሶሻል ክስረት አዘቅት ከግምት በላይ ነው።

በአገሪቱ ችግሮች በዝርዝር ከተወያየ በኋላ 21ኛው የአኢተማ ዓመታዊ ጉባኤ የሚ ከተሉትን ውሳኔዎች አሳለፈ።

1:— አምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት ተጠቦ ፕሮግራም አውጥቶ፤የጊዜውን ችግሮች፤ሲሆን አስቀድሞ አለዚያም በችግሩ ወቅት ከመፍታት ይልቅ በው ጭ ኃይል፤በሶቭየት እየተመራ፤አንድ ጊዜ እረገጋለ ዘመቻ ሌላ ጊዜ የ ምርት ዘመቻ እያለ፤ሕዝቡ በራሱ ቀረት ከጣለው ችግር ጋር የሚያደር ገውን ትግል በማደናቀፍ ስለሚያምሰው፤ይህ አምባገነን መንግሥትና አማ ካሪው፤የበላይ ተጠባባቂው የሶቭየት መንግሥት፤ለዚህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለደረሰው ችግር ተጠያቂዎች ናቸው ብሎ ያምናል።

2:— አምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት የቢሮክራቲክ ክበርቴ መደብ እንደመሆ ኑ ሁሉ የዚህን መደብ ጥቅም የመንግሥት እርሻ፤የመንግሥት ንግድ ድር ሻ ወዘተ በመንግሥት ካፒታሊዝም (State Capitalism) ይዘ ት ስለሚጠብቅ፤የመንግሥት በሥልጣኖችንና የበላይ ተጠባባቂ ጌቶቹው ን ኪስ ስለሚሞላ ይህ ጉባኤ ያወግዘዋል።

3:— በዚህ አምባገነን ወታደራዊ መንግሥት አገዛዝ የተበዘበዙ ገበሬ፤ወዝ አደር፤የልዩ ልዩ ሙያ ሠራተኞች፤ዲሞክራቶች፤አገር ወዳዶች ወዘተ በአ ንድ ላይ በመነሳት ይህንን ሥርዓት ከሥር መሰረቱ ገንቅለው ካልጣሉ አገራችን ከምትገኝበት የፖለቲካ፤የኢኮኖሚና የሶሻል ክስረት መላቀቅ እንደማትችል ይህ ጉባኤ ያምናል።ለዚህም ጥሪ ያደርጋል።ኢአተማ ለ ዚህ ግብ እንደሚታገል ያረጋግጣል።

## ስለ ፖለቲካ እሥረኞች

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ እያለ ዘመን በፊውዳሊዝም የበዝባዥ ቀንበር ሥር ወድቆ ሲማቅቅ በነበረበት ጊዜ፤በሆነ ባልሆነው ምክንያት እሥር ቤት እየተወረወረ፤ከኩሽናው ውስ ጥ አብዛኛውን ዘመን በእሥር ቤት ውስጥ የሚያሳልፈው ሰው ቁጥር ቀላል አልነበረም።ይሁ ንና ዛሬ አምባገነኑና ትምክህተኛው የወታደር መንግሥት የሰፊውን ሕዝብ አብዮት ቀልብሶ የራሱን አምባገነንነት ለማስፈን በሚያደርገው ቀረት፤ፀረ—ዲሞክራሲነትን የሚቃወሙ፤የኢኮኖ ሚ ውድቀትን የሚቃወሙ፤የጦርና የውስጥ ፖለቲካ መበላሸትን (ሰብተኝነትን) የሚቃወሙ፤የ ብሔረሰቦች የራስን እድል በራስ መወሰን መብት መታፈኑን የሚቃወሙ፤ብሔራዊ ነፃነት መደፈ ሩን የሚቃወሙ፤በአጠቃላይ ዲሞክራት፤አገር ወዳድ፤ለእኩልነት ታጋይ፤ወዘተ ምሁር፤ወጣት፤ወ ዝአደር፤ገበሬ፤መለዮ ለባሽ፤ቤት፤ወዘተ እየታፈነ ያለ አንዳች ፍርድ እሥር ቤት እንዲወረ ወር በማድረጉ፤በአገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ እሥረኛ ቁጥር ብቻ ከ40000 በላይ መሆኑ ይነ ገራል።ስለሆነም ይህ ጉባኤ:—

1:— ይህ አምባገነንና ትምክህተኛ መንግሥት የሚያካሂደውን ፀረ—ሕዝብ እ ሥራት በጥብቅ ያወግዛል።

2:— ይህን ፀረ—ሕዝብ ድርጊት ለዓለም አቀፍ ሰላም ወዳጆችና ታጋዮች ያ ለ አንዳች ማቋረጥ ያጋልጣል።

3:— በአገሪቱ ውስጥ እየበረከቱ በመጡት ወህኒ ቤቶች ውስጥ ታጉረው የሚ ጉሳሉት ከላይ የተጠቀሱት የፖለቲካ እስረኞች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይ ጠይቃል።ለዚህም ይታገላል።

## ስለ ፖለቲካ ስደተኞች

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከዕለት ዕለት እየጠመረ በመጣው የፖለቲካ፤የኢኮኖሚና የሶ ሻል ጭቆና ምክንያት፤በተለይም የራስ እድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ለማስከበር የሚታ ገሉትን ብሔረሰቦች ትግል ለማፋፈን በሚደረገው ጭፍን የትምክህተኛ ጭፍጨፋ ምክንያት፤ቤቱን

ኅብረቱን፣ዘመዱን፣ጓደኛውን እየተወ ከትውልድ አገሩ የሚሰደደው ሰው ቁጥር በየዕለቱ እየጨመረ ነው፡፡ከዚህ የተነሳ ከሦስት ሚሊዮን የበለጠ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በስደት ላይ ይገኛሉ፡፡ይህም አገሪቱን በዓለም ላይ በስደተኛ አፍሪነት አሰውቋታል፡፡ስለሆነም፡—

1. ይህ ጉባዔ ይህን ለሕዝቦች መሰደጃ ምክንያት የሆነ የአምባገነንና የትምክህተኛ አስተዳደር በጥብቅ ያወግዛል፡፡

2. ኢኢተማ ስደተኞችን ለመርዳት ጥረት ከሚያደርጉ ልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር አቅሙ አስከቻለ ድረስ እንደሚተባበር ያበስራል፡፡

3. ኢኢተማ እነዚህ በከፍተኛ ቁጥር ከትውልድ አገራቸው ተሰደደው በልዩ ልዩ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያኖች፣በያሉበት የመኖር መብታቸውን ለማስከበር እንዲሁም ወደ ትውልድ አገራቸው ተመልሰው በሰላምና በክብር ለመኖር በሚያደርጉት ትግል ኢኢተማ ከጎናቸው ተሰልፎ እንደሚታገል ያረጋግጣል፡፡

## ስለ ብሔረሰቦች

ዛሬ ኢትዮጵያ ተብላ በምትጠራው አገር ውስጥ ብዙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ልዩ ልዩ ባህልና ልዩ ልዩ ሃይማኖት ያላቸው ሕዝቦች ይኖሩበታል፡፡እነዚህን ሕዝቦች በአንድ የጭቆና ቀንበር ሥር ያኖራቸው አንድነት በሕዝብ ፍላጎት የተመሰረተ ሳይሆን የገዢዎች የብዝበዛ ወረራ የወለደው ነው፡፡

በዚህ ያለውዴ በግድ አንድነታቸው የእርስ በርስ መፈቃቀድና መቀራረብ እንዳይዳብር የገዢው መደብ ለከፋፍሎ መግዛት እንዲያመቸው የአንዱን ባሕል ከሌላው ከፍ፣የአንዱን ቋንቋ ከሌላው ዝቅ በማድረግ መጠነኛ ቢሆንም በመካከላቸው ቅራኔ እንዲኖር አድርጓል፡፡ ሆኖም ደግሞ በዚሁ በግዴታ አንድነታቸውና በአንድ የጭቆና ቀንበር ሥር በመኖራቸው አንድ የሚያደርጓቸው ሁኔታዎች ብዙ ናቸው፡፡የሁሉም ብሔረሰብ ፍላጎት ብዝበዛ የሌለበት ሥርዓት መገንባት፣በሌላው ብሔር ባሕልና ቋንቋ ተፅዕኖ ሥር ሳይወድቅ የራሱን ባሕልና ቋንቋ ማበልፀግ፣በመፈቃቀድና በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድነትን መመሥረት፣ለዘመናት ከተጫነበት ድህነት፣በሽታና ድንቁርና ተላቆ ለሚከተለው ትውልድ ቀስትና ያለው የኑሮ ስልት መፍጠርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ይህን ለማሟላት የሚደረገው ትግል አረጅምና መራራ ነው፡፡ይህ ሃቅ በአብዮት ታሪክ ተገልጧል፡፡የአብዮት ታሪክ የሚያስረዳው የትግሉን ረጅምነትና መራራነት ብቻ ሳይሆን፣የመጨረሻ አሸናፊ ጭቁን ሕዝቦች መሆናቸውንም ጭምር ነው፡፡ኢ.ኢ.ተ.ማ እነዚህን በወረራ አንድ የሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በግዴታ ጋብቻቸው ዘመን ውስጥ ያፈሯቸውን አንድ የሚያደርጓቸውን ሁኔታዎች አያቀሳቸውም፡፡እንዲያውም ከፍተኛ ሥፍራ ይሰጣቸዋል እንጂ! በጣሊያን ፋሺስት ላይ የተገኘው ድል፣የኃይለ ሥላሴ ፋሺስታዊ መንግሥት እንደ አምባይ ካብ መፈረረስ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ድል ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድ ላይ መታገል መቻላቸውን የሚያሳይ ምስክርም ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድነት ከነዳቸው የኃይለ ሥላሴን ፋሺስታዊ መንግሥት አፈራርሰው የእኩልነትና የመከባበር ኑሮ ሲጠብቁ በሥፍራ የተተካው አምባገነን ወታደራዊ መንግሥት ትምክህተኝነትን መረን አስለቀቀ ጭቆናዎችን በአለህበት ሂድ ብቻ ሳይሆን የባሰ አዘቅት ውስጥ ጥሏቸዋል፡፡በዚህም የተነሳ በየማዕዘኑ ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን መሣሪያ አንስተው በዱር በገደሉ ይቀደዳሉ፡፡ስለሆነም፡—

1:— ኢ.ኢ.ተ.ማ የብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል ድረስ ያውቃል፡፡ለዚህ መብት መከበር ከጭቁን ብሔረሰቦች ጎን ተሰልፎ ይታገላል፡፡

2:— በኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ጭቆናን ለማጥፋት፣የራስን እድል በራስ ለመወሰን የሚያካሂዱትን ትግሎች ሙሉ በሙሉ ይደግፋል፡፡

3:— ትምክህተኛውና አምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት በጭቁን ብሔረሰቦች ላይ የሚያካሂደውን ጭፍጨፋ በጥብቅ ያወግዛል፡፡



4:— አምባገነኑና ትምክህተኛው ወታደራዊ መንግስት በኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚገኙ ጭቁን ሕዝቦች መካከል ከልጅ ልጅ የሚቀረስ ቂም ለማጋባት፡—
ሀ. አንዱን ብሔረሰብ በሌላው ብሔረሰብ ምድር ላይ በማስፈር
ለ. አንደኛውን ብሔረሰብ በሌላው ላይ በማዝመት የሚያካሂደውን ሴራ በጥብቅ ያወግዛል፡፡

5:— ኢ.ኢ.ተ.ማ በ19ኛው ጉባዔው ላይ ለኤርትራ፣ለኦሮሞ፣ለአፋር፣ለቢዓማ እንዲሁም ለሌሎች የብሔረሰብ ታጋዮች የሰጠውን ድጋፍ አሁንም ያድሳል፡፡

6:— ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝቦች የሚገዛው ትምክህተኛ ወታደራዊ መንግስት ጸንጻሉን የሶቭየትን መንግስት ከነዱ የተመረኮዘና እስከ ጥርሱ የታጠቀ እንደመሆኑ መጠን በተናጠል ትግል ብዙ እንደማይበገር ይገመታል ስለሆነም የብሔረሰቦች ታጋዮች እንዲሁም ሌሎች ተራማጆች በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የትግል አንድነት ፈጥረው ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ኢ.ኢ.ተ.ማ.ጥሪ ያደርጋል፡፡

## ስለ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት፣የብሔረሰብ ነቅናቄ ድርጅቶችና እንዲሁም ገለሰቦች መፍጠር ስለአለባቸው የትግል አንድነት፡—

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ከሠላሳ ዓመት በማያንስ እድሜው ውስጥ ታሪክ ሊረሳቸው የማይገባው አያሌ ነጥቦች አሉበት፡፡በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ ጎን ቆሞ ባደረገው መራራ ትግል የኃይለ ሥላሴን ፋሺስታዊ መንግሥት በዓለም ፊት እንዴት ራቁቱን እንዳስቀረው የሚረሳ አይደለም፡፡ከዚያም በላይ ተማሪና ምሁር ከጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተዋህዶ፣ከሕዝቡ ተማር መልስህም አስተምር፣ከሕዝቡ ጋር ሆነህ አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመሥረት ታገል በሚል መርሆ ያፈራቸው አብዮታውያን በአመኑበት ዓላማ ቆመው ለዴሞክራሲ፣ለእኩልነት፣ለብሔራዊ ነፃነት መከበር፣ለሰብአዊና ለኢኮኖሚ ብልጽግና እንዴት እንደታገሉና ደማቸውን እንዳፈሰሱ ታሪክ ለዘላለም የሚረሳው አይደለም፡፡

እስከ 1974 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ከሞላ ጎደል ኢትዮጵያውያኖችን ሁሉ በአንድነት ይዞ የሚታገል ድርጅት እንደነበረና የትግል ድምፁም በተቀነበረ ሁኔታ የሚያስተጋባና ተሰሚነቱ ከፍ ያለ ድርጅት እንደነበረ ይታወቃል፡፡ከ1974 ወዲህ ባለው ዘመን ውስጥ በአገሪቱ ውስጥ በተካሄደው ከፍተኛ የመደብ ትግልና በአምባገነኑ መንግሥት ትምክህተኛ እርምጃ አንዱም የኢትዮጵያ ተማሪዎች መለያየትን ቢያስከትል ሌላ ደግሞ የጭቁን ብሔረሰብ ወገኖችን ደግሞ ተለይተው እንዲደራጁ አድርጓቸዋል፡፡

ምንም እንኳን እነዚህን ልዩ ልዩ የተማሪ ድርጅቶች በተለያየ መፈክር ሥር ቢሰለፉም የሚታገሉት አንድ ጠላት፣አምባገነኑንና ትምክህተኛውን የወታደር መንግሥት ነው፡፡ይሁንና ይህ የተናጠል ትግል የጠላትን ክፍል አላሸበረውም፡፡እንዲያውም ፋታ ስለሰጠው በውጭም በውስጥም የተማሪን እንቅስቃሴ ለማጥፋት አያሌ አረመኔ እርምጃዎች ወስዷል፡፡የተማሪዎች ፓስፖርት መከልከል፣ከሚበረሩበት አገር (በምሥራቅ አውሮፓ ላሉ) እንዳይወጡ መከልከል፣የትምህርት አበላቸው እየተቋረጠ እንደበረሩ ማድረግ፣ታፍነው ለቅጣት ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ማድረግ፣ወዘተ በተደጋጋሚ የተሞከሩ ዘዴዎች ናቸው፡፡

ዛሬ የዚህን አምባገነን መንግሥት ወንጀል በከፍተኛ ደረጃ ለማጋለጥና የሰፊውን ሕዝብ ትግል ውጤት በሚታይ ሁኔታ ለማስተጋባት እነዚህን ልዩ ልዩ የተማሪ ድርጅቶች በመካከላቸው ያለውን መጠነኛ ቅራኔዎች አቻችለው የትግል አንድነት መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

ይህ 21ኛ የኢ.ኢ.ተ.ማ ጉባዔ፣ መጭው የኢ.ኢ.ተ.ማ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከልዩ ልዩ የተማሪ ማህበራትና ከብሔረሰብ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በማድረግ

1:— ባሉት የልዩነት ነጥቦች ላይ በሰፊና ዴሞክራቲክ ውይይት በማካሄድ መግባባት የሚገኝበትን ዘዴ እንዲሸ፣

2:— ስምምነት በተገኘባቸው ነጥቦች ላይ በአንድነት የመታገል ችሎታ እንዲፈጠር፣

3:— ዛሬ በየቦታው ተበታትነው የሚገኙት ኢትዮጵያውያኖች ተሰባስበው በጋራ የትግል መድረክ ውስጥ ይሰለፉ ዘንድ ልዩ ልዩ ድርጅቶች በየበኩላቸው ጥረት እንዲያደርጉ፣እንቅሙ እስከተፈቀደለት ድረስ እንዲተባበር ያሰበል::

## ስለ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ሕብረት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር፣በውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲደራጁ የአረጅም ጊዜ ትግል እንዳካሄደ አይዘነጋም::በ1978 ይህ ትግል ፍሬን በመስጠት ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃ በልዩ ልዩ ሀገራት ተደራጅተው የሚገኙ የተማሪ ድርጅቶች አንድ ላይ በመሰብሰብ፣በዲሞክራሲ ላይ የተመሰረተ የዓለም አቀፍ የተማሪዎች ማህበር ከነፌደሬሽን መቋቋሙ ይታወሳል::ይህ አብዮታዊ የትግል መድረክ መፈጠር፣በሀገሩ ውስጥም ሆነ በውጭ ለሚገኙ ሀቀኛ ተራማጆችና ለብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም በቅንነት ለሚታገሉ ኃይሎች ከፍተኛ የሞራል ድጋፍን ቢሰጥ፣በአንፃሩ የኢትዮጵያን አብዮት ለሚቃወሙ ኃይሎች (በአጠቃላይ) መረበሽን አስከትሏል::እንዲሁም በውጭ ሀገር የሚገኙ ተራማጅ ዲሞክራትና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሊሰባሰቡ የሚችሉበትን መድረክ ፈጥሯል::

ምንም እንኳ በዚህ ፌደሬሽን መፈጠር በውጭ የሚገኙ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲ፣ብሔራዊ ነፃነት፣ፍትህና ሰብአዊ መብት እንዲሁም ለብሔረሰቦች እኩልነት በሚታገሉ ኃይሎች ዘንድ ከፍተኛ አብዮታዊ አስተዋፅዖ ቢጠበቅበትም ቅሉ፣በተለያዩ ምክንያቶች የተጠበቀውን ያህል የሥራ ፍሬ ለማየት አልተቻለም::እንደሚታወቀው፣ከብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ጋር ቀስ በቀስ መቀልበስ፣የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያለሙትና የፈለጉት የዲሞክራሲና የብልፅግና ኑሮ በተግባር አልታየም::ይልቁንስ ዛሬ ሰፊው ሕዝብ በትግሉ ያገኛቸው ድሎች ሙሉ በሙሉ ተቀልብሰው፣በብሔራዊ ውርደት፣በረሀብ፣በስደት፣በዲሞክራሲ መጥፋትና በጭፍጨፋ ዓለም ውስጥ በአሻንጉሊት ወታደራዊ መንግሥትና ገብረ አበሮች ተገዶ እንዲኖር ሆኗል::

ዛሬ በአምባገነኑ ወታደራዊ መንግሥት በአገሪቱ ውስጥ በሚካሄደው ከፍተኛ ጭፍጨፋ የተነሳ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አገራቸውን እየለቀቁ በስደት በባዕድ አገር እየተንገላቱ መኖራቸው ይታወቃል::ከዚህ ጋር ተያይዞ በውጭ የሚገኘውን የተቃውሞ ኃይል ለማዳከም አምባገነኑ መንግሥትና በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች በቀጥታ ከመንግሥታት ጋር በመተባበር፣በዚህ አገር በሚገኙ ዲሞክራቲክ፣አገር ወዳድ እንዲሁም ተራማጅ ኃይሎችን ያቀፈ የተማሪ ማህበራትንና የጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት በማስገፈፍ፣ቀጥተኛ ተፅዕኖ ለማድረግ በማይቻልበት የምዕራብ አውሮፓ አገሮች ፓስፖርትን አሳዶስም በማለት የኢትዮጵያነት መብታቸውን በመገፈፍ በውጭ የሚገኘውን ተቃውሞ ልክ እንደ አገር ቤቱ አዳፍኖ ለማስቀረት ያልተቋረጠ ጭቆና በማካሄድ ላይ ይገኛል::ይህ በአገር ቤትና በውጭ ሀገር ተጣምሮ የሚካሄደው ከፍተኛ ጭቆናን ለመከላከል፣በአንድ ወገን የጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች በየቦታው ቢደራጁ፣በሌላ በኩል ገና አያሌ ያልተደራጁ ኃይሎች፣የዲሞክራሲ መጥፋት፣ብሔራዊ ነፃነት መገርሰስ፣የጭቁን ብሔረሰቦች በአምባገነኑ መንግሥትና ገብረ አበሮች መጨፍጨፍ የሚያስቆጣቸው፣በየቦታው ተበታትነው ይገኛሉ::ስለሆነም ዛሬ ባለው ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ በውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ተራማጅ፣ዲሞክራትና ሀገር ወዳድ ኃይሎች ኃይላቸውን መሰብሰብና ትግላቸውን ማስተባበር የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን፣በዚህ በኩል ከዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌደሬሽን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይጠበቅበታል::ይህ 21ኛው የአ.ኢ.ተ.ማ ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ ጥያቄ ላይ ያሳለፈውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ:—

ሀ:— የዓለም አቀፍ ፌደሬሽን በአስቸኳይ አማካይ ቦታ ፈልጎ የሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤውን እንዲጠራ፣ማሰባሰብ፣

ለ:— መጪው ሥራ አስኪያጅ ከጽሕፈት ቤቱ ጋራ የጠበቀ ግንኙነትን በማድረግና በተለይም ላይ በተዘረዘሩት ጥያቄዎች ላይ እህት ማህበራት ሊያበረክቱ የሚችሉትን አስተዋፅዖ በየጊዜው ውይይት በማድረግ በአጭር ጊዜ መፍትሄ ሊያገኙ የሚያስችላቸውን መንገድ አብሮ መተለም፣



ሐ:— ከእህት ማህበራት ጋር በመተባበር ጽሕፈት ቤቱ በየጊዜው አዳዲስ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ላይ መግለጫዎችን በማውጣት፣

መ:— ከእህት ማህበራት ጋር በመተባበር፣በውጭ በስደተኝነት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት የሚቻልበትን ዘዴ ለመፈለግ፣በሌላ ወገን ደግሞ ከፌደሬሽኑ ውጭ ተደራጅተው የሚገኙ የተማሪ ድርጅቶችና የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች ጋር የትብብር መድረክ ለመክፈት (ለመፍጠር) የሚቻልበትን ሁኔታ ማጥናት፣

ሠ:— በማህበር ያልተደራጁ ኢትዮጵያውያን (ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች) እንዲደራጁ ቅስቀሳ እንዲያካሂዱ፣ የ21ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በመወያየት መጪው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር በመተባበር ወደ ሥራ የሚተረጉምበትን ዘዴ እንዲሸ አብዮታዊ ጥሪውን ያስተላልፋል::